# ጣሃራ፣ ሶላትና የቀብር ስነ-ስርዓት

በ ሼኽ:ሙሐመድ ቢን ሳልሕ ቢን ዑሰይሚን

ሁዳ ፕሪስ ሊሚትድ

Kingdom of Saudi Arabia
The Cooperative Office for call and Guidance
to Communities at Al Ma'azar & Um Al-Hammam
Under the Supervision of the Ministry of Islamic Affairs
Endowment Guidance & Propagation
Tel: 4826466 - Fax: 4827489 - P.O.Box: 31021 Riyadh: 11497

20

ሸይኽ ሙሐመድ ብን ሷሊሕ አልዑሠይሚን

# ጦሃራ ሶላት

እና

# የቀብር ሥነሥርዓት

አሳታሚ - ሁዳ ኘሬስ ሊሚትድ
የመጀመሪያ እትም
1989

Copyright HUDA PRESS Ltd. 1417 A.H. /1996

All rights reserved. No part of this publication may be reproduced, stored in a retrieval system, or transmitted in any form or by any means, electronic, mechanical, photocopying, recording or otherwise, without the prior permission of the copyright owner.

# ምዕራፍ 1

# ጦሃራ (ንጽሕና)

* ውዱእ
* የገላ ትጥበት
* ተየሙም
* ጫማ ላይ ማበስ (መስሑል–ኹፍፈይን)
* የታመመ ሰው የጦሃራ (ንጽሕና) አፈጻጸምና አሰጋገድ

# ውዱእ

ውዱእ እንደ ሽንት፣ ዓይነምድር፣ በዓይነምድር መውጫ በኩል ከሆድ የሚወጣ አየር፣ ጥልቅ እንቅልፍና የግመል ሥጋ[1] መብላት ያለ ትጥበቱን ግዴታ የሚያደርግ መለስተኛ ክስተት (አል–ሐደሥ አል–አስገር) ሲከሰት የሚ ፈጸም የግዴታ ጠሃራ ትጥበት ነው።

¤ የውዱእን ትሩፋት አስመልክቶ የሚከተሉት ሐዲሦች ተላልፈዋል:-
ከዑመር (ረዐ) በተላለፈው ትረካ ነቢዩ (ሰዐወ) እንዲህ ብለዋል:-

عن النبي، ﷺ، أنه
قال: «ما منكم من أحدٍ يتوضأ فيسبغ الوضوء، ثم يقـول: أشهـد أن لا إله إلا الله وحده لا شريك له وأشهـد أن محمـدًا عبده ورسوله، اللهم اجعلني من التوابين واجعلني من المتطهرين، إلا فُتحت له أبواب الجنة الثمانية يدخل من أيها شاء».

«ከናንተ መካከል ውዱእ አድርጎ ውዱኡን ያሟላና ከዚያም ‹አሽሀዱ አን ላእላሀ እልላልኋህ ወሕደሁ ላ ሸሪከ ለሁ፤ ወአሽሀዱ አንነ ሙሐመደን ዐብዱሁ ወረሱሉሁ አልኋሁምመ እጅዐልኒ ምነት–ተዉዋቢን፣ ወጅዐልኒ ምነል–ሙተጠ ህሪን፤› [ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ እንደሌለና እሱ ብቸኛውና ሸሪክ የሌለው መሆኑን እመሰክራለሁ፤ ሙሐመድ አገልጋዩና መልእክተኛው መሆናቸውንም እመሰክራለሁ፤ አላህ ሆይ! (ከኃጢአታቸው ተጸጽተው) ወደ አንተ ከሚመለሱት አድርገኝ፤ በብዙ ከሚጥራሩት (ከሚጽዳዱትም) አድርገኝ፤] ያለ ሰው ስምንቱ የጀነት መግቢያ በሮች ተከፍተውለት በፈለገው (በር) ይገባል።»[2]

¤ ከዑሥማን (ረዐ) በተላለፈው ትረካ ደግሞ ነቢዩ (ሰዐወ) እንዲህ ብለዋል:-

---

1 ይህ በሐንበሊ መዝሀብ መሆኑን አንባቢ ሊያውቅ ይገባል–ተርጓሚው

2 ሙስሊምና ትርምዚ ያጠናቀሩት

«من توضأ فأحسن الوضوء خرجت خطاياه من جسده حتى تخرج من تحت أظفاره» رواه مسلم.

«ውዱእ አድርጐ ውዱኡን ያሳመረው ሰው ኃጢአቶቹ ከጥፍሮቹ ሥር እንኳ ሳይቀር ከአካላቱ ይወጣሉ።»[1]

¤ ከዐሊይ ብን አቢ ጧሊብ በተላለፈው መሠረት ነቢዩ (ሰዐወ) እንዲህ ብለዋል:-

«إسباغ الوضوء على المكاره، وإعمال الإقدام إلى المساجد، وانتظار الصلاة بعد الصلاة يغسل الخطايا غسلاً».

«(በብርድና በመሳሰሉት) እየከበደ ውዱእን አሟልቶ መፈጸም፣ እግሮችን ወደ መስጊዶች ማራመድና ከአንዱ ሶላት በኋላ ሌላውን ለመስገድ መጠባበቅ ኃጢአቶችን በሚገባ ያጥባል።»

## የውዱእ አደራረግ ሁኔታ

1. በአንደበት ሳይናገሩ ውዱእ ለማድረግ በልብ ቁርጠኛ ውሳኔ (ኒያ) ማድረግ፤ በምላስ ኒያን መናገር ያላስፈለገው ነቢዩ (ሰዐወ) በውዱአቸው፣ በሶላታቸውም ሆነ በማናቸውም የአምልኮተ–አላህ (ዕባዳ) ክንዋኔዎቻቸው ውስጥ ኒያ ሲያደርጉ በምላሳቸው ያልተናገሩ በመሆናቸውና አላህ(ሱወ) ልብ ያሰበውን ስለሚያውቅ ያሰቡትን ለርሱ መንገር አስፈላጊ ባለመሆኑ ነው።
2. ከዚያም በአላህ ስም በመጀመር «ብስምልላህ» ማለት፣
3. ከዚያም ሁለቱን መዳፎች ሦስት ጊዜ ማጠብ፤
4. ከዚያም ሦስት ጊዜ መጉመጥመጥና በአፍንጫ ውሃ ስቦ ማስወጣት፤
5. ከዚያም ፊትን በአግድም ከጆሮ እስከ ጆሮ ከላይ ጸጉር ከቆመበት ጀምሮ ወደታች ከአገጭ በታች ድረስ አዳርሶ ሦስት ጊዜ ማጠብ፤
6. ከዚያም እጆችን ከጣቶች ጫፍ እስከ ሁለቱ ክርኖች ድረስ በቀኙ ጀምሮ ግራውን በማስከተል ሦስት ጊዜ ማጠብ፤
7. ከዚያም እጆቹን አርጥቦ ከግንባሩ በላይ አንሥቶ ወደ ማጅራቱ ራሱ ላይ በማሳረፍና ከዚያም ወደ ፊት በመመለስ አንድ ጊዜ ራስን ማበስ፤

---

1 በሙስሊም የተጠናቀረ

8. ከዚያም አመልካች ጣቶቹን በጆሮዎቹ ቀዳዳዎች ውስጥ በማስገባትና በአውራ ጣቶቹ የጆሮዎቹን የውጭኛ ክፍል አንድ ጊዜ ማበስ፤
9. ከዚያም ሁለት እግሮቹን ከጣቶች ጫፍ እስከ ሁለቱ ቁርጭምጭሚቶች ድረስ በቀኙ እግር ጀምሮ ግራውን በማስከተል ሦስት ጊዜ ማጠብ፤

## የገላ ትጥበት (ጉስል)

**የገላ ትጥበት (ጉስል)**:- እንደ ሩካቤ ሥጋ ግንኙነት (ጀናባህ) እና የወር አበባ (ሐይድ) መጥቶ መሄድ ያለ ገላን የመታጠብ ግዴታ የሚያስከትል አቢይ ክስተት (አል–ሐደሡል–አክበር) ሲከሰት የሚፈጸም ግዴታ (ዋጅብ) የሆነ ጦሃራ ነው።

## የገላ ትጥበት አፈጻጸም

1. ገላ ለመታጠብ በምላስ ሳይናገሩ በልብ ኒያ ማድረግ፤
2. ከዚያም በአላህ ስም በመጀመር «ብስምልላህ» ማለት፤
3. ከዚያም የተሟላ ውዱእ ማድረግ፤
4. ከዚያም በራሱ ላይ ማፍሰስና በደንብ ካረጠበው በኋላ ሦስት ጊዜ በራሱ ላይ ማፍሰስ፤
5. ከዚያም የተቀረውን የገላውን ክፍል ማጠብ፤

## ተየሙም

**ተየሙም**:- ውሃ ያጣ ወይም ውሃ መጠቀም ለጉዳት የሚዳርገው ሰው በውዱእና በገላ ትጥበት (ጉስል) ፈንታ በአፈር የሚደረግ ግዴታ (ዋጅብ) የሆነ ጦሃራ ነው።

## የተየሙም አደራረግ

ተየሙም የሚያደርገው በውዱእ ይሁን ወይም በገላ ትጥበት (ጉስል) ምትክ የቱ እንደሆን ለይቶ ኒያ ማድረግና መዳፎቹን በመሬት ገጽ ወይም እንደ ግድግዳ ባለና ከመሬት ጋር በተያያዘ ነገር ላይ በማሳረፍ በመዳፎቹ ፊቱንና እጆቹን ማበስ ነው።

## ጫማዎች ላይ ማበስ (አል–መስሑ ዐለል–ኹፍፈይን )

‹ኹፍፍ› ወይም ጫማ ሲባል ማለት የተፈለገው ከቆዳና ከመሳሰሉት የተሠራ ሆኖ እግር የሚጠለቅበትና የሚሸፈንበት ሽፋን ማለት ነው። ‹ጀዋርብ› ወይም የግር ሹራቦች ሲባል ደግሞ ማለት የተፈለገው ከጥጥና ከመሳሰሉት ነገሮች ተሠርቶ እግር ላይ የሚለበስ ካልሲ ለማለት ነው።

ጫማዎችና ካልሲዎች ላይ ማበስን የሚመለከት ደንብና ማበስ ሕጋዊ ለመ ሆኑ ከቁርአንና ሱንና የተወሰደ ማስረጃ:-

በጫማዎቹ ላይ ማበስ ከአላህ መልዕክተኛ (ሰዐወ) የተላለፈ ሱንና ሲሆን ጫማ ወይም የእግር ሹራብ የለበሰ ሰው ውዱእ ሲያደርግ አውልቆ እግሩን ከመታጠብ የጫማዎቹን ወይም የእግር ሹራቦቹን የላይኛ ክፍል በእጅ አበስ አበስ ማድረጉ የበለጠ ይሆናል። ለዚህ ማስረጃው የሙጊራ ብን ሹዕባህ ሐዲሥ ነው።

¤ ሙጊራ በተረኩት መሠረት ነቢዩ(ሰዐወ) ውዱእ እያደረጉ ወደ እግሮች ትጥበት ሲደርሱ ጫማዎቻቸውን ላወልቅላቸው ጐንበስ ስል:-

«دعهما فإني أدخلتهما طاهرتين»

«ተዋቸው ንጹሕ ሆነው (ከታጠብኩኝ በኋላ) ነው ያስገባኋቸው» አሉና በእ ጃቸው የጫማዎቻቸውን የላይኛ ክፍል አበሱ ብለዋል።

በውዱእ ወቅት ሁለቱን እግሮች ከጫማ አውጥቶ ከማጠብ ይልቅ ጫማዎ ቹን ሳይፈቱ በእጅ ማበስ ሕጋዊነቱ በአላህ መጽሐፍ –በቁርአን– እና በአላህ መልዕክተኛ (ሰዐወ) ሱንና የጸና ነው።

የሕጋዊነቱ ማስረጃ ከቁርአን የሚከተለው የአላህ (ሱወ) ቃል ነው:-

﴿يا أيها الذين آمنوا إذا قمتم إلى الصلاة فاغسلوا وجوهكم وأيديكم إلى المرافق وامسحوا برؤوسكم وأرجلَكم إلى الكعبين﴾

«እናንት ያመናችሁ ሆይ! ወደ ሶላት በቆማችሁ (ለመቆም ባሰባችሁ) ጊዜ፥ ፊቶቻችሁን፥ እጆቻችሁንም፥ እስከ ክርናች እጠቡ። ራሶቻችሁንም (በውሃ) እበሱ። እግሮቻችሁንም እስከ ቁርጭምጭሚቶች (እጠቡ)፤...»[1]

በላይኛው አያህ ውስጥ በአማርኛ «..እግሮቻችሁንም» ተብሎ የተተረ ጐመው وأرجُلَكُم ‹ወአርጁለኩም› وأرجُلِكُم እና ‹ወአርጁልኩም› የሚሉና ከአላህ መልዕክተኛ (ሰዐወ) መተላለፋቸው የተረጋገጠ ሁለት ዓይነት ‹ቅራአህ› (አነባብ) አለው። በአንደኛው አነባብ መሠረት እግሮቻችሁንም እጠቡ የሚል ትርጉም ይሰጣል። በሁለተኛው አነባብ ደግሞ «..ራሶቻችሁንም (በውሃ) እበሱ..» ከሚለው ጋር በመጣመር እግሮቻ ችሁንም በውሃ እበሱ የሚል ፍቺ ይሰጣል። ሁለቱ እግሮች በውዱእ ወቅት ሊታጠቡም በውሃ ሊታበሱም መቻላቸውን ያብራራው የነቢዩ (ሰዐወ) ሱንና ነው። ነቢዩ (ሰዐወ) እግሮቻቸው ከጫማ ውጭ በሆኑ ጊዜ ውዱእ ካደረጉ ያጥቧ ቸው የነበረ ሲሆን ውዱእ ሲያደርጉ ጫማ አድርገው ከሆነ ግን የጫማዎቻቸውን የላይኛ ክፍል በእጅ ያብሱ ነበር።

የሐዲሡን ማስረጃ በተመለከተ በዚህ ረገድ ከአላህ መልዕክተኛ በስፋት የተዘገቡ ሐዲሦች ይገኛሉ። ኢማም አሕመድ (ረዐ) «ማበስን በተመለከተ ልቤ ውስጥ ምንም ጭንቀት የለም፣ ከአላህ መልዕክተኛ (ሰዐወ) እና ከሰሓባ የተላለፉ አርባ ሐዲሦች አሉና» ብለዋል። የ‹መስሑል–ኹፍፈይን» ሐዲሥ ‹ሙተዋትር› ወይም በስፋት ከተዘገቡ ታዋቂ ሐዲሦች መካከል አንዱ መሆኑን አስመልክቶ ከተቋጠሩ ስንኞችም የሚከተሉትን እናገኛለን።

---

1 አል–ማእዳህ (5: 6 )

በስፋት ከተዘገቡ ታዋቂ ሐዲሦች መካከል
‹መን ከዘበ ዐለይያ..» የሚለውን አንድ በል
‹መን በና ልላህ..» የሚል ሐዲሥ አስከትል
የሙእምናች ጌታቸውን ማየት በወዲያኛው ሕይወት
የ‹ሩእያህ› የ‹ሸፋዓ› ሐውድንም የሚመለከት
የ‹መስሑል–ኹፍፈይን› ሐዲሥም ‹ሙተዋትር›ነው በስፋት

ይህ ጫማ ላይ ማበስን አስመልክቶ ከቁርአንና ከነቢዩ (ሰዐወ) ሐዲሥ የተወሰደ ማስረጃ ነው።

## ጫማዎች ላይ ለማበስ መሟላት ያለባቸው ነጥቦች (ሹሩጥ)

በውዱእ ጊዜ እግሮችን ከጫማ ማውጣት ሳያስፈልግ በማጠብ ፈንታ ጫሞቹ ላይ ለማበስ አራት ነገሮች መሟላት አለባቸው:-

አንደኛው መመዘኛ– ጫማው የተደረገው ወይም የእግር ሹራቡ የተለበሰው ከ ‹ጠሃራ› በኋላ መሆን፤ ለዚህ ማስረጃው:-

«دعهما فإني أدخلتهما طاهرتين».

«ተዋቸው! ንጹሕ ሆነው (ከታጠብኳቸው በኋላ) ነው ያስገባኋቸው» በማለት ነቢዩ (ሰዐወ) ለሙጊራ የተናገሩት ሐዲሥ ነው።

ሁለተኛው መመዘኛ– የሁለቱ ጫማዎች ወይም የእግር ሹራቦች ንጹሕ (ጣህር) መሆን፤ ንጽሕና የሌላቸው ነጃሳ ከሆኑ ግን በላያቸው ላይ ማበሱ አይፈቀድም። ለዚህ ማስረጃው የአላህ መልዕክተኛ (ሰዐወ) አንድ ጊዜ ሰሓባቸውን በመምራት ሶላት ሲሰግዱ በሶላቱ መሐል ጫማቸውን በማውለቅ ጫማዎቹ ቆሻሻ ወይም ጉድፍ ነገር እንዳለባቸው መልአኩ ጅብሪል የነገራቸው መሆኑን መናገራቸው ነው። ይህም ቆሻሻ ወይም ነጃሳ ባለበት ነገር መስገድ የማይፈቀድ መሆኑን ያመለክታል። ቆሻሻው በውሃ ከታበሰ አባሹ በቆሻሻው ስለሚበከል ንጹሕ የመሆን ብቃት የለውም።

ሶስተኛው መመዘኛ–ጫማዎቹ ወይም የእግር ሹራቦቹ የሚታበሱት ገላን የመታጠብ ግዴታ ከሚያስከትሉ ከግብረ ሥጋ ግንኙት በኋላ እንደሚፈጸ

መው የ‹ጀናባ› ትጥበት ባሉ አቢይ ክስተት (ሐደሡል–አክበር) ሳይሆን የውዱእ ግዴታን በሚያስከትለው መለስተኛ የትጥበት ክስተት (በውዱእ) ጊዜ ብቻ መሆኑ አንዱ መመዘኛ ነው።

አራተኛው መመዘኛ–ማበሱ የሚያገለግለው በሸሪዓው ተወስኖ ለተደነገገ የጊዜ ገደብ ብቻ መሆን አበለት። ይህም ለነዋሪ ሰው አንድ ቀንና ሌሊት ሲሆን በእንግድነት ላይ ለሚገኝ መንገደኛ (ሙሳፊር) ግን ሦስት ቀናት ከነሌሊቶቻቸው ነው። ይኸውም ዐሊይ እብን አቢ ጧሊብ (ረዐ):-

النبي ، ﷺ ، للمقيم يومًا وليلة وللمسافر ثلاثة أيام ولياليهن ، يعني في المسح على الخفين أخرجه مسلم .

«ነቢዩ (ሰዐወ) ለነዋሪ ሰው አንድ ቀንና ሌሊት፣ ለመንገደኛ ደግሞ ሦስት ቀናት ከነሌሊቶቻቸው አድርገዋል። ማለትም በሁለቱ ጫማዎች ላይ ማበስን በተመለከተ»[1]

ዐ ሊ በማለት በተላለፈው መሠረት ነው። ይህ ጊዜ አንድ ሰው ከተሟላ ትጥበት በኋላ ጫማዎቹን ካደረገ በኋላ አንስቶ ለነዋሪ ሃያ አራት ሰዓት ሲሆን ለመንገደኛ ደግሞ ሰባ ሁለት ሰዓት ነው። አንድ ሰው ማክሰኞ ዕለት ለፈጅር ሶላት አስፈላጊውን ትጥበት አሟልቶ ንጽሕናው (ጠሃራው) ሳይፈርስ እስከ ማታ ድረስ ቆይቶ ዕሻ ሶላት ሰግዶ ቢተኛና ከዚያ በኋላ ለሱብሕ ሶላት በአሥራ አንድ ሰዓት ተነስቶ ጫማዎቹ ላይ ቢያብስ ጊዜው የሚጀምረው ከረቡዕ ጧት አሥራ አንድ ሰዓት ሆኖ እስከ ሐሙስ ጧት አሥራ አንድ ሰዓት ድረስ ይዘልቃል። ሐሙስ ከአሥራ አንድ ሰዓት በፊት ጫማዎቹ ላይ ያበሰ ቢሆን የሐሙስ ማለዳ የሱብሕ ሶላት በዚሁ ሊሰግድ ይቻለዋል። በተጨማሪም ውዱእ እስካልፈረሰ ድረስ የተወሰነው የጊዜ ገደብ ቢያበቃ እንኳ ያሻውን ያህል መስገድ ይችላል። ይህም ሚዛን በደፋው የዕውቀት ባለቤቶች አቋም መሠረት ነው። የአላህ መልዕክተኛ (ሰዐወ) ለይተው የወሰኑት በጫማዎቹ ላይ የታበሰው የሚያገለግልበትን የጊዜ ገደብ እንጂ የጠሃራውን የጊዜ ገደብ አይደለም። ስለዚህም የተወሰነው የጊዜ ገደብ ካበቃ በኋላ ሌላ ማበስ አይኖርም። ግን

1 ሙስሊም ያጠናቀሩት

ጠሃራውን ካላፈረሰው ጠሃራው እንደጸና ይቆያል። ይህ ጠሃራ በሸሪዓው ማስረጃ መሠረት የጸና ስለሆነና በሸሪዓዊ ማስረጃ የጸና ነገር ያለ ሌላ ሸሪዓዊ ማስረጃ (ደሊል) ሊሻር አይችል ልም። የ‹መስሑ› የአገልግሎት ጊዜ በመሙላቱ ውዱኡ ይፈርሳል የሚል ማስ ረጃ (ደሊል) ደግሞ የለም። ከዚህም በላይ በመርሑ መሠረት የነበረን ነገር የሚያስወግደው ነገር መኖሩ ካልተገለጸ በስተቀር እንደነበረ ይቆያል። እነኚህ ለ‹መስሑል–ኹፍፈይን› መሟላት ያለባቸው መሥፈርት (ሹሩጥ) ሲሆኑ አንዳንድ የዕውቀት ባለቤቶች የጠቀሷቸው ሌሎች ሸርጦችም ይገኛሉ፤ አንዳንዶቻቸው ግን መጤን የሚኖርባቸው ናቸው።

## የታመመ ሰው አስተጣጠብ

1. የታመመ ሰው ውዱእ በማድረግ ከመለስተኛው የርከሰት ክስተት መጽዳትና ገላውንም በመታጠብ ከአቢይ የርከሰት ክስተት መጽዳት ይኖርበታል።

2. በመድከሙ ወይም በሽታው ይባባስብኛል ወይም የመዳኛውን ጊዜ ያራዝም ብኛል ብሎ በመስጋት በውሃ መታጠብ ካልቻለ ግን ተየሙም ያደርጋል።

3. የተየሙም አደራረጉም በሁለት እጆች ንጹሕ የመሬት ገጽ አንድ ጊዜ በመምታት (በማሳረፍ) በሁለት እጆቹ ፊቱን ሙሉ በሙሉ ማበስና ከዚያም ሁለቱን እጆቹን አንዱ በሌላ እርስበርሳቸው ማበስ ነው።

4. ለራሱ ጦሃራ ማድረግ ካቃተው ሌላ ሰው ውዱእ ወይም ተየሙም ያደር ግለታል።

5. ጦሃራ ሊደረግለት በሚገባ አንድ አካሉ ላይ ቁስል ቢኖር በውሃ ያጥባል። በውሃ ማጠቡ የሚያሳምመው ከሆነ እጁን በውሃ አርሶ ላዩ–ላይ በማሳለፍ አበስ አበስ ያደርጋል። ማበሱም የሚያሳምመው ከሆነ ለዚያ አካል ፈንታ ተየሙም ያደርጋል።

   ከአካላቱ በአንዱ ላይ ስብራት ደርሶ በጨርቅ ወይም በጀሶ የታሰረ ከሆነ በዚያ አካል ላይ በማጠብ ፈንታ በውኃ ያብሰዋል፤ ተየሙም ማድረግ አያስፈልግም ማበስ ማጠቡን ይተካልና።

7. በግድግዳ ላይ ወይም በሌላ ንጹሕ ሆኖ አቧራ ባለው ነገር ላይ ተየሙም ማድረግ ይፈቀዳል። ግድግዳው ቀለም በመሳሰለና አፈር ባልሆነ ነገር የተለሰነ ከሆነ ግን አፈር እስከሌለው ድረስ ተየሙም አይደረግበትም።

8. መሬት ገጽ ላይ ወይም ግድግዳ ላይ ወይም ሌላ አፈር ባለው ነገር ላይ ተየሙም ማድረግ ካልተመቸ አፈር በእቃ ወይም በመሐረም ተደርጐ ከዚያ ተየሙም ቢደረግበት ምንም የለበትም።

9. ለአንድ ሶላት ተየሙም አድርጐ ተየሙሙ ሳይፈርስ የሌላ ሶላት ወቅት ቢደርስ በዚያ በመጀመሪያው ተየሙም ይሰግዳል። ተየሙሙን የሚያፈርስ ነገር ስላልተከሰተና ጠሃራው እንደነበረ ስላለ ለሶላቱ ዳግም ተየሙም አያደርግም። ከወሲባዊ ተራክቦ በኋላ ለጀናባ ተየሙም አድርጐ ከሆነ ገላን የመታጠብ ግዴታ የሚያስከትል ሌላ የጀናባ ትጥበት ግዴታ ካልተከሰተ ሌላ ተየሙም እንደገና አያደርግም። ይሁን እንጂ በዚህ ጊዜ ውስጥ የመለ ስተኛ ትጥበት (የውዱእ) ግዴታ የሚያስከትል ሁኔታ ከተከሰተ ግን ተየሙም ያደርጋል።

10. የታመመ ሰው ገላውን ከርክሰቶች ማጽዳት ያለበት ሲሆን መታጠብ ካልቻለ ግን ባለበት ሁኔታ ይሰግዳል፤ ሶላቱን በዳነ ጊዜ መድገም አይፈለ ግበትም።

11. የታመመ ሰው መስገድ ያለበት ንጹሕ (ጣሂር) በሆነ ልብስ ነው። ልብሶቹ በርክሰት ከተበከሉ ማጠብ ወይም ሌላ ንጹሕ ልብስ መቀየር አለበት። ካልተመቸው ግን ባለበት ሁኔታ ይሰግዳል። ሶላቱን በዳነ ጊዜ መድገም አይፈለግበትም።

12. በሽተኛው ንጹሕ በሆነ ሥፍራ ላይ መስገድ ያለበት ሲሆን መስገጃው ከተበከለ ግን ማጠብ ወይም ንጹሕ በሆነ ሌላ መስገጃ መለወጥ ወይም ንጹሕ የሆነ ነገር በላዩ—ላይ ማንጠፍ ይኖርበታል። ካልተመቸው ግን ባለበት ሁኔታ ይሰግዳል። ሶላቱም ብቁ ሆኖ ስለሚቆጠር መድገም አይፈለግበትም።

13. የታመመ ሰው መታጠብ ወይም ተየሙም ማድረግ ስለ አቃተው ሶላትን ከጊዜው ማዘግየት አይፈቀድለትም። የተቻለውን ያህል ጠሃራ ያደርግና በገ ላው በልብሱ ወይም በመስገጃው ላይ ማስወገድ የሚያቅተው ርክሰት (ነጃሳ) ቢኖር እንኳ ሶላቱን በወቅቱ ይሰግዳል። አላህ (ሱወ) እንዲህ ብሏልና:-

﴿فاتقوا الله ما استطعتم﴾

«አላህንም የቻላችሁትን ያክል ፍሩት!...»[1]

14. አንድ ሰው ሽንቱ በማያቋርጥ ሁኔታ የሚፈስ ሆኖ ከተቸገረ ለሶላት ውዱእ የሚያደርገው የሶላቱ ጊዜ ከገባ በኋላ መሆን አለበት። የግዴታው ሶላት ወቅት ሲደርስ መሸኛውን ይታጠብና ልብስና ገላው እንዳይበከል ብልቱን በንጹሕ ነገር ይጠቀልልና ውዱእ አድርጎ ይሰግዳል። ለሁሉም የግዴታ ሶላቶች ይህንኑ ይከተላል። አስቸጋሪ ሆኖ ከከበደው ዙህርና ዐስር አንድ ላይ ወይም መግሪብና ዕሻን አንድ ላይ አጣምሮ (ጀምዕ አድርጎ) መስገድ ይፈቀድለታል። ግዴታ ላልሆኑ ተጨማሪ (ነፍል) ሶላቶች ግን ወቅቱ የፈርድ (ግዴታ) ሶላት ወቅት ካልሆነ በተመሳሳይ ሁኔታ ውዱእ ያደርግና ይሰግዳቸዋል። ወቅቱ የፈርድ ሶላት ከሆነ ግን ለፈርድ ሶላቱ ያደረገው ውዱእ በቂው ሆኖ በዚያው ይሰግዳቸዋል።

## የታመመ ሰው እንዴት እንደሚሰግድ

1. የታመመ ሰው የግዴታ ሶላትን በግድግዳ ላይ ተደግፎ ወይም አስፈላጊ ከሆነ በትር ተመርኩዞም ቢሆን ቁሞ መስገድ አለበት።
2. መቆም ያቃተው ከሆነ ግን ተቀምጦ ይሰግዳል። በሚቆምበትና ሩኩዕ በሚያደርግበት ቦታ ላይ እግሮቹ ላይ ቁጥጥ ብሎ መቀመጥ ይመረጣል።
3. ተቀምጦ መስገድ የማይችል ከሆነ ፊቱን ወደ ቅብላ በማድረግ በጐኑ እንደ ተኛ ይሰግዳል። በቀኝ ጐኑ ላይ መሆኑ ይመረጣል። ፊቱን ወደ ቅብላ መመለስ ካልተመቸውም ባለበት ሆኖ ይሰግዳል። ሶላቱም ትክክለኛ ሆኖ ስለሚቆጠር መድገም አያስፈልገውም።
4. በጐኑ ተኝቶ መስገድ ካቃተው በጀርባው እንደተኛ እግሮቹን ወደ ቅብላ በመመለስ ይሰግዳል። ወደ ቅብላ አቅጣጫ ለማየት ራሱን ትንሽ ቀና ማድረግ በላጭ ነው። ካልቻለ ግን እግሮቹ ወደ ቅብላ ይሆኑና ባለበት ሁኔታ ይሰግዳል። በዚህ ሁኔታ የሰገደው ሶላት በቂ ሆኖ ስለሚቆጠር መድገም አያስፈልገውም።

---

1 አል–ተጋቡን (64):16

5. በሽተኛው በሶላቱ ውስጥ ሩኩዕ እና ሱጁድ ማድረግ ያለበት ሲሆን ካልቻለ ግን በራሱ ምልክት ያደርጋል። ለሱጁድ ራሱን ከሩኩዕ ይበልጥ ዝቅ ያደርጋል። ሩኩዕ ማድረግ ችሎ ሱጁድ ካቃተው ለሱጁድ በራሱ ምልክት ያደርጋል። ሱጁድ እንጂ ሩኩዕ ማድረግ የሚያቅተው ከሆነ በሩኩዕ ጊዜ ራሱን በማዘቅዘቅ ምልክት ይጠቀማል።

6. በሩኩዕና በሱጁድ በራስ ምልክት መስጠት ካቃተው በዐይኖቹ ምልክት በመስጠት ለሩኩዕ በመጠኑ ዓይኖቹን ይጨፍናቸዋል፣ ለሱጁድ ደግሞ ይበልጥ ይጨፍናቸዋል። አንዳንድ በሽተኞች እንደሚያደርጉት ዓይነት በጣቶች ምልክት መስጠቱ ግን ትክክለኛ አይደለም። ከክታብና ከሱንናም ሆነ ከዓሊሞች ቃል መሠረት አላገኘሁለትም።

7. በራስ ማመልከት ወይም በዓይን ማመልከት ያልቻለ ከሆነ በልቡ (በሃሳቡ) ይሰግድና በልቡ ተክቢራ አድርጎ ምንባቡን፣ ሩኩውን፣ ሱጁዱን፣ መቆምና መቀመጡንም በልቡ ያስባል። እያንዳንዱ ሰው የልቡን ቁርጠኛ ሃሳብ ውጤት ያገኛልና።

8. በሽተኛው እያንዳንዱን ሶላት በወቅቱ መስገድና ማድረግ ከሚገባው ውስጥ መፈጸም የቻለውን ሁሉ መፈጸም አለበት። እያንዳንዱን ሶላት በወቅቱ መስገድ ካቃተው ዙህርና ዐስርን መግሪብና ዕሻን በአንደኛቸው ጊዜ በጥምረት (ጀምዕ) መስገድ ይችላል። ይህም ዐስርን በዙህር ወቅት፣ ዕሻን በመግሪብ ጊዜ አስቀድሞ በመስገድ ነው። ወይም ደግሞ ዙህርን ወደ ዐስር፣ መግሪብንም ወደ ዕሻእ በማዘግየት ሁለቱን አመቺ በሚሆንለት ጊዜ አጣምሮ መስገድ ነው። የሱብሕ ሶላት ግን ከበፊቱ ባለውም ሆነ ከኋላው ከሚመጣው ሌላ ሶላት ጋር በጥምረት አይሰገድም።

9. በሽተኛው ከአገሩ ወጥቶ በእንግድነት የሚታከም ከሆነ ባለ አራት ረክዓ ሶላቶችን በማሳጠር (በቐስር) ዙህር ዐስርና ዕሻ ሶላቶችን ሁለት ሁለት ብቻ ይሰግዳል። ይህም የመቆያው ጊዜ አጠረም ረዘመ ወደ አገሩ እስከሚመለስበት ጊዜ ድረስ ነው።

# ምዕራፍ 2

# ሶላት

* ትሩፋቱና አስፈላጊነቱ
* አፈጻጸሙ
* የመርሳት ሱጁድ (ሱጁድ አስሰህዉ)
* የቁርአን ምንባብ ሱጁድ (ሱጁድ አት–ቲላዋህ)
* ሶላት የማይሰግድን ሰው የሚመለከት ሕግ
* ንስሐ (ተውባህ)

**ሶላት**:- ከእስላም ማዕዘናት ውስጥ አንዱ ማዕዘን ሲሆን ከቃለ ተውሒድ (ከሁለቱ ቃለ ምስክርነት) በኋላ በጣም ጥብቁ የእስላም ማዕዘን ነው።

**ሶላት**:- አላህንና አገልጋይ ባሪያውን የሚስተሳስር መገናኛ ነው።

¤ ነቢዩ (ሰዐወ) እንዲህ ብለዋል:-

إن أحـدكم إذا صلى يناجي ربه

«አንዳችሁ በሚሰግድበት ጊዜ ወደ ጌታው ነው የሚያኾከሽከው»[1]

● አላህ (ሱወ)፣ ነቢዩ (ሰዐወ) ባስተላለፉት ሐዲሥ አል–ቁድሲ ውስጥ እንዲህ ብሏል:-

الحـديث القـدسي: قسمت الصلاة بيني وبين عبدي نصفين، ولعبدي ما سأل، فإذا قال العبد: الحمد لله رب العالمين قال الله تعالى: حمدني عبدي. وإذا قال: الرحمن الرحيم قال الله تعالى: أثنى عليَّ عبدي، وإذا قال: مالك يوم الدين قال: مجَّدني عبدي، فإذا قال: إياك نعبـد وإياك نستعين قال: هذا بيني وبين عبدي ولعبدي ما سأل، فإذا قال: اهد نا الصراط المستقيم صراط الذين أنعمت عليهم غير المغضوب عليهم ولا الضالين قال: هذا لعبدي ولعبدي ما سأل

«ሶላትን በኔና በአገልጋዩ መካከል ሁለት ቦታ ከፍያለሁ፣ አገልጋዩም የጠየቀውን ያገኛል። አገልጋዩ:- ‹አል–ሐምዱ ሊልላህ ረብብል–ዓለሚን› (ምሥጋና የዓለማት ሁሉ ጌታ ለሆነው ለአላህ ይሁን) ባለ ጊዜ፣ አላህ (ሱወ) ‹ባሪያዬ አመሰገነኝ› ይላል። ‹አር–ረሕማንር–ረሒም› ሲልም ‹ባሪያዬ አወደሰኝ› ይላል። ‹ማሊክ

1 ቡኻሪ የዘገቡት

የውምድዲን› (የፍርዱ ቀን ባለቤት ለሆነው) ሲልም ‹ባሪያዬ ኃያልነቴን አወሳ› ይላል። ‹እይያከ ነዕቡዱ ወእይያከ ነስተዒን› (አንተን ብቻ እንገዛለን! አንተንም ብቻ እርዳታ እንለምናለን) ባለ ጊዜም ‹ይኽ በኔና በባሪያዬ መካከል ሲሆን ለባሪያዬ የጠየቀው አለለት› ይላል። ‹እህድነስ–ሲራጠል–ሙስተቂም ሲራጠል ለዚነ አንዐምተ ዐለይህም ጓይሪል–መግዱብ ዐለይህም ወለድዷል–ሊን› (ቀጥተኛውን መንገድ ምራን። የነዚያን በነሱ ላይ በጐ የዋልክላቸውን፣ በነርሱ ላይ ያልተቆጣህባቸውንና ያልተሳሳቱትንም ሰዎች መንገድ ምራን) ሲልም ‹ይህ የባሪያዬ ነው፣ ለባሪያዬም የጠየቀውን እሰጠዋለሁ› ይላል።[1]

**ሶላት** :- የዕባዳ (አምልኮተ–አላህ) ዓይነቶች በሁሉም መልካቸው ያለቡት የአትክልት ሥፍራ ነው። ሶላት የሚጀመርበት ተክቢራ (አሏሁ አክበር) እና ሰጋጁ የአላህን ቃል የሚያነበንብበት ቀጥ ብሎ መቆም (ቅያም)፣ የፈጣሪ ጌታ ስም የሚያከብርበትና የሚያወድስበት ሩኩዕ፣ የአላህ ወሰን የለሽ ምሥጋና የሚያጥለቀልቀው ከሩኩዕ ተመልሶ ቀና ማለት (እዕትዳል)፣ የአላህን ኃያልነትና ልዕልና በማጥራት በጸሎት የሚማጸንበት ሱጁድ፣ ለዱዓእና ለ‹ተሸሁድ› መቀመጥና በሠላምታ ሶላቱን ማጠቃለል፣...እነኚህ ሁሉ የዕባዳ ዓይነቶች የተካተቱበት የዕባዳ መድረክ ነው።

**ሶላት**:- አሳሳቢ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ አጋዥ፣ ከክፉና ከመጥፎ ነገሮች ከልካይ ነው።

● አላህ (ሱወ) እንዲህ ብሏል:-

قال الله تعالى: ﴿واستعينوا بالصبر والصلاة﴾. وقال تعالى: ﴿اتلُ ما أُوحي إليك من الكتاب وأقم الصلاة إن الصلاة تنهى عن الفحشاء والمنكر﴾.

«በመታገሥና በሶላትም ተረዱ!..»[2]

«ከመጽሐፉ ወደ አንተ የተወረደውን አንብብ! ሶላትንም ደንቡን ጠብቀህ ስገድ! ሶላት ከመጥፎና ከሚጠላ ነገር ሁሉ ትከለክላለችና!..»[3]

---

1 ሙስሊም የዘገቡት

2 አል–በቀራህ (2):45

3 አል–ዐንከቡት (29):45

**ሶላት**:- ልቦቻቸው ውስጥ የሚፈነጥቅና በትንሣኤው ቀን ወደ ጌታቸው በሚሰበሰቡበት የፍርዱ ቀን የሚበራላቸው ብርሃን ነው።

¤ ነቢዩ (ሰዐወ) እንዲህ ብለዋል:-

النبي ، ﷺ : الصلاة نور(١) وقال: مَن حافظ عليها كانت له نورًا وبرهانًا ونجاة يوم القيامة(٢).

«ሶላት ብርሃን ነው»[1]

«አዘውትሮ ለሰገደው ሰው በትንሣኤ ቀን ብርሃን፣ ማስረጃና መድህን ይሆንለታል»[2]

**ሶላት**:- የምእመናን ልባዊ ደስታቸውና የዐይናቸው ማረፊያ ነው።

¤ ነቢዩ (ሰዐወ) እንዲህ ብለዋል:-

«جعلت قرة عيني في الصلاة»

«የዓይኔን ማረፊያ ሶላት አደረገው»[3]

**ሶላት**:- የኃጢአቶች ማበሻና የጥፋት ማካካሻ ነው።

¤ ነቢዩ(ሰዐወ) እንዲህ ብለዋል:-

النبي ، ﷺ : «أرأيتم لو أن نهرًا بباب أحدكم يغتسل فيه كل يوم خمس مرات هل يبقى من درنه (وسخه) شيء؟ قالوا لا يبقى من درنه شيء، قال فكذلك مثل الصلوات الخمس يمحو الله بهن الخطايا»

---

1 ሙስሊም የዘገቡት

2 አሕመድ፣ እብን ሕባን እና ጠበራኒ የዘገቡት

3 አሕመድና ነሳኢ የዘገቡት

«አንደኛችሁ ከደጃፉ ወንዝ (ጅረት) ቢኖርና በቀን አምስት ጊዜ ቢታጠብበት አንዳች እድፍ ይቀርበታልን ንገሩኝ ? ...‹የለም ምንም እድፍ አይቀርበትም› አሉ። ይህ እንግዲህ አላህ ኃጢአቶችን የሚያብሰባቸው የአምስቱ ሶላቶች ተምሣሌት ነው።»[1]

وقـال، ﷺ : «الصلوات الخمس والجمعة إلى الجمعة كفارة لما بينهن ما لم تغشَ الكبائر»

«አምስቱ ሶላቶችና ከጁሙዓ እስከ ጁሙዓ፣ ከባዳዎቹ ኃጢአቶች (ከባእር) ካልተፈጸመ በመካከላቸው ለሚከሰቱ መለስተኛ ጥፋቶች ማበሻ ናቸው።»[2]

صلاة الجماعة أفضل من صلاة الفذ بسبع وعشرين درجـة ،

«በሕብረት የሚሰገድ (የጀማዓ) ሶላት በነጠላ ከሚሰገደው በሃያ ሰባት ደረጃ ይበልጣል።»[3]

مَن سرَّه أن يلقى الله غدًا

مسلمًا فليحافظ على هؤلاء الصلوات حيث ينادي بهن فإن الله تعالى شرع لنبيكم سنن الهدى وإنهن من سنن الهـدى، ولـو أنكم صليتم في بيوتكم كما يصـلي هذا المتخلف في بيتـه لتركتم سُنَّـة نبيكم، ولو تركتم سنَّة نبيكم لضللتم، وما من رجل يتطهر فيحسن الطهور ثم يعمد إلى مسجد من هذه المساجد إلا كتب الله له بكل خطوة يخطوهـا حسنة، ويرفعه بها درجة ويحطُّ عنه بها سيئـة، ولقـد رأيتنا وما يتخلف عنها إلا منافق معلوم النفاق، ولقد كان الرجل يؤتى به يهادي بين الرجلين حتى يقام في الصف

---

1 ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት

2 ሙስሊም የዘገቡት

3 ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት

«ነገ አላህን ሙስሊም ሆኖ መገናኘት የሚወድ ሰው ጥሪ (አዛን) በሚደረግበት የሕብረት ሶላት መስገጃ ሥፍራ በመገኘት እነኚህን ሶላቶች አዘውትሮ በትጋት ይስገድ። አላህ (ሱወ) ለነቢያችሁ የመመሪያ መንገዶችን (ሱነኑል–ሁዳ) የደነገላቸው ሲሆን እነኚህ ሶላቶች ከነዚህ አንዱ ናቸው። እቤቱ ቀርቶ ብቻውን እንደሚሰግደው ሰው እቤቶቻችሁ ከሰገዳችሁ የነቢያችሁን ሱንና(ፈለግ) ትተዋላችሁ። የነቢያችሁን ሱንና ከተዋችሁ ደግሞ በርግጥ ትሳሳታላችሁ። ተጣጥቦና ውዱኡን አሟልቶ ከመስጊዶች ወደ አንደኛቸው የመጣ ሰው በሚራመደው እያንዳንዱ እርምጃ አላህ ምንዳ ይጽፍለታል፣ ደረጃውን ከፍ ያደርግለታል፣ ኃጢአቱን ይሰርዝለታል። ከጀማዓ ሶላት፣ አስመሳይ መናፍቅነቱ በግልጽ ከታወቀበት ሰው በስተቀር ማንም አይቀርም ብለን እናስብ ነበር። አንድ ሰው ታሞ ቢሆን እንኳ በሁለት ሰዎች መካከል ተደግፎ ወዲህና ወዲያ እያጋደለ ተይዞ መጥቶ ሶላት ሶፍ (ረድፍ) እንዲቆም ይደረግ ነበር።»[1] ብለዋል– እብን መስዑድ(ረዐ)።

በሶላት ውስጥ ሃሳብን በርሱ ላይ ብቻ በማሰባሰብ መመሰጥ (ኹሹዕ) ማዘውተር ጀነት ለመግባት መረማመጃ ከሚሆኑ ምክንያቶች አንዱ ነው።

● አላህ (ሱወ) እንዲህ ብሏል:-

قال الله تعالى: ﴿قد أفلح المؤمنون. الذين هم في صلاتهم خاشعون. والذين هم عن اللغو معرضون. والذين هم للزكاة فاعلون. والذين هم لفروجهم حافظون إلا على أزواجهم أو ما ملكت أيمانهم فإنهم غير ملومين. فمن ابتغى وراء ذلك فأولئك هم العادون. والذين هم لأماناتهم وعهدهم راعون. والذين هم على صلواتهم يحافظون. أولئك هم الوارثون الذين يرثون الفردوس هم فيها خالدون﴾.

---

1 ሙስሊም የዘገቡት

«ምእመናን ፍላጐታቸውን ሁሉ በእርግጥ አገኙ፤ (ዳኑ)። እነዚያ እነሱ በስግደ ታቸው ውስጥ፤ (አላህን) ፈሪዎች፤ እነዚያም እነሱ ከውድቅ ንግግር ራቂዎች፤ እነዚያም እነሱ ዘካን ሰጪዎች፤ እነዚያም እነሱ ብልቶቻቸውን ጠባቂዎች፥ የኾኑት (አገኙ)። በሚስቶቻቸው፥ ወይም እጆቻቸው በያዟቸው (ባሪያዎች) ላይ ሲቀር፥ እነሱ (በነዚህ) የማይወቀሱ ናቸውና። ከዚህም ወዲያ የፈለጉ ሰዎች፥ እነዚያ እነሱ ወሰን አላፊዎች ናቸው። እነዚያም፥ እነሱ ለአደራዎቻቸውና ለቃል ኪዳናቸው ጠባቂዎች፤ እነዚያም እነሱ በስግደቶቻቸው ላይ የሚጠባበቁ፤ የኾኑት (አገኙ)፤ እነዚያ ወራሾቹ እነርሱ ናቸው፤ እነዚያ ፊርደውስን (ላዕላይ ገነትን) የሚወርሱ ናቸው፤ እነሱ በርሷ ውስጥ ዘውታሪዎች ናቸው።»[1]

ሶላት ውስጥ ልቦናን ለአላህ (ሱወ) ፍጹም በማድረግ በነቢዩ ሱንና ውስጥ በተመለከተው መሠረት መስገድ ሶላቱ አላህ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው ለማድረግ ሁለቱ መሠረታዊ መሥፈርት ናቸው።

¤ ነቢዩ (ሰዐወ) እንዲህ ብለዋል:-

«إنـما الأعـمال بالنيـات وإنما لكل امرىء ما نوى»

«ሥራዎች በልባዊ ውሳኔዎች (ንይያህ) ላይ የተመረኮዙ ናቸው። እያንዳንዱ ሰው የልቡን (የንይያውን) ያገኛል።»[2]

«صلوا كما رأيتموني أصلي»

«እኔ ስሰግድ ባያችሁኝ መሠረት ስገዱ»[3]

## ሶላት

ሶላት አንደበታዊና አካላዊ ክፍሎች ያሉት፤ በተክቢራ (አሏሁ አክበር) ተጀምሮ በተስሊም (አስሰላሙ ዐለይኩም) የሚጠቃለል ዕባዳ (አምልኮተ–አላህ) ነው።

---

1 አል–ሙእምኑን (23): 1–11

2 ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት

3 ቡኻሪ የዘገቡት

አንድ ሰው መስገድ ሲፈልግ የውዱእ ግዴታ የሚያስከትል መለስተኛ ርክ ሰት ካለበት ውዱእ ማድረግ ወይም ገላን የመታጠብ ግዴታ የሚያስከትል አቢይ ርክሰት ካለበት ገላውን መታጠብ አለበት። ውሃ ካላገኘ ወይም በውኃ መታጠቡ ጉዳት የሚያስከትልበት ከሆነ ተየሙም ያደርጋል። ገላውን ልብሱንና የመስገጃ ሥፍራውን ከቆሻሻ ማጽዳት አለበት።

## የሶላት አሰጋገድ ሁኔታ

1. ያለ መዛነፍና ያለመዞር ሰውነቱን ሙሉ በሙሉ ወደ ቅብላ ማዞር፤
2. ከዚያ መስገድ የሚፈልገውን ሶላት በምላሱ ሳይናገር በልቡ በማሰብ ቁርጠኛ የመስገድ ውሳኔ (ንይያህ) ማድረግ፤
3. የሶላት መግቢያ ተክቢራ (ተክቢረቱል–እሕራም) በማድረግ ‹አሏሁ አክበር› ማለትና በዚህ ጊዜ ሁለት እጆቹን በትከሻዎቹ ትይዩ ወደላይ ማንሳት፤
4. ከዚያም የቀኝ መዳፉን በግራ መዳፉ የውጭ ጀርባ ላይ በማድረግ ደረቱ ላይ መያዝ፤
5. ከዚያም የሚከተለውን የመክፈቻ ጸሎት ማለት:-

«سبحانك اللهم وبحمدك، وتبارك اسمك، وتعالى جدك، ولا إله غيرك».

«ሱብሐነከ አሏሁምመ ወቢሐምድከ ወተባረከ እስሙከ ወተዓላ ጀድዱከ ወላእላሀ ጓይሩከ»

ትርጉሙ :- «አሏህ ሆይ! ጥራትና ምሥጋና ይገባሀ፣ ስምህ ቅዱስ ነው። ገርማህና ኃያልነትህ ላቀ፣ ካንተ በስተቀርም ሌላ አምላክ የለም» ማለት ነው።

«اللهم باعد بيني وبين خطاياي كما باعدت بين المشرق والمغرب. اللهم نقني من خطاياي كما يُنقّى الثوب الأبيض من الدنس. اللهم اغسلني من خطاياي بالماء والثلج والبَرَد».

«አሏሁምመ ባዕድ በይኒ ወበይኑ ኽጣያየ ከማ ባዐድተ በይነል–መሽሪቕ ወል–መግሪብ፤ አሏሁምመ ነቅቕኒ ምን ኽጣያየ ከማ ዩነቐቋ አሥ–ሠውቡል–አብየዱ ምነድ–ደነስ፤ አላሁምመ እግስልኒ ምን ከጣያየ ብል–ማእ ወሥ–ሠልጅ ወል–በረድ»

ትርጉሙ:- «አላህ ሆይ! በኔና በኃጢአቶቼ መካከል ምሥራቅና ምዕራብን እንዳራራከው አራርቅ። አላህ ሆይ! ነጭ ልብስ ከእድፍ እንደሚነጻው ሁሉ እኔንም ከኃጢአቶቼ አንጻኝ። አላህ ሆይ! ከኃጢአቶቼ በውሃ በበረዶና በዝናም በረዶ እጠበኝ።» ማለት ነው።

6. ከዚያም ተዐዉውዝ በማድረግ :-

«أعوذ بالله من الشيطان الرجيم».

«አዑዙ ብልላህ ምነሽ–ሸይጣነር–ረጂም»

ትርጉሙ:- «ከተረገመው ሸይጣን በአላህ እጠበቃለሁ» ማለት ነው።

7. ቀጥሎም በበስመላህ በመጀመር ፋቲሐህ በማንበብ እንዲህ ማለት:-

«بسم الله

الرحمن الرحيم، الحمد لله رب العالمين. الرحمن الرحيم. مالك يوم الدين. إياك نعبد وإياك نستعين. اهدنا الصراط المستقيم. صراط الذين أنعمت عليهم غير المغضوب عليهم ولا الضالين».

«አልሐምዱ ሊልላህ ረብቢል–ዓለሚን። አር–ረሕማን–ርረሒም። ማሊከ የውምድ–ዲን። እይያከ ነዕቡዱ ወእይያከ ነስተዒን። እህድነስ–ስራጠል–ሙስተቚም ሲራጠል–ለዚነ፤ አንዐምተ ዐለይሀም፤ ጎይረል–መግዱብ ዐለይሀም፤ ወለድ–ዷልሊን።»

ትርጉሙ:- «ምስጋና ለአላህ ይገባው፣ የዓለማት ጌታ ለሆነው፣ እጅግ በጣም ርህሩህ በጣም አዛኝ፣ የፍርዱ ቀን ባለቤት ለሆነው። ለአንተ ብቻ እንገዛለን፣ አንተንም ብቻ እርዳታ እንለምናለን። ቀጥተኛውን መንገድ ምራን። የነዚያን በነርሱ ላይ በጐ የዋልክላቸውን በነሱ ላይ ያልተቆጣህባቸውንና ያልተሳሳቱትንም ሰዎች መንገድ (ምራን በሉ)።» ማለት ነው።[1] ከዚያም «آمين» አ–ሚ–ን (አላህ ሆይ ተቀበልልን ስማን) ይላል።

8. ቀጥሎም ከቁርአን የተመቸውን ያህል ያነብና በሱብሕ ሶላት ምንባቡን ረዘም ያደርጋል።

9. ከዚያም ለአላህ ክብር ከወገቡ ወደፊት በመታጠፍ ያጐነብሳል። በዚህ ሩኩዕ ጊዜ ሁለት እጆቹን በትከሻዎቹ ትይዩ ከፍ በማድረግ አሏሁ አክበር ይላል። ሱንናው ከወገቡ እጥፍ ብሎ ወደፊት በማዘንበል ራስን ከወገብ አቅጣጫ በማስተካከል ጣቶች ዘርዘር ያሉ ሆነው በሁለቱ እጆች ሁለቱን ጉልበቶች መያዝ ነው።

10. በሩኩዕ ወቅት ሦስት ጊዜ :- «سبحان ربي العظيم»

«ሱብሓነ ረብብየል–ዐዚም» (ሀያል ለሆነው ጌታዬ ጥራት ተገባው) ይላል።

«سبحانك اللهم وبحمدك اللهم اغفر لي»

«ሱብሓነከ አልሏሁምመ ወብሐምድከ አልሏሁምመ እግፍርሊ» (አሏህ ሆይ ጥራትና ምሥጋና ይድረስህ፣ አሏህ ሆይ ማረኝ) የሚል ቢጨምርበት ጥሩ ነው።

11. ከዚያም «ሰምዐልሏሁ ልመን ሐምደህ» «سمع الله لمن حمده» (አሏህ የአመስጋኙን ምሥጋና ሰማ) እያለ ሁለት መዳፎቹን በትከሻዎቹ ትይዩ እያነሳ ከሩኩዕ ቀና ይላል። በኢማም ተመርቶ የሚሰግድ ተከታይ (መእሙም) ግን «ሰምዐልሏሁ ልመን ሐምደህ» አይልም። በዚህ ፈንታ «ربنا ولك الحمد». «ረብበና ወለከል–ሐምዱ» (ጌታችን ሆይ ምሥጋና ላንተ ይሁን) ይላል።

12. ከዚያም ራሱን ቀና ካደረገ በኋላ:-

1 አል–ፋቲሐ 1: 1–7

«ربنا ولك الحمد. ملء
السموات وملء الأرض وملء ما شئت من شيء
بعد».

«ረብበና ወለከል–ሐምዱ፤ ምልአስሰማዋት ወምልአል–አርድ፣ ወምልአ ማሸእተ ምን ሸይእን በዕድ» ይላል።

ትርጉሙ:- «ጌታችን ሆይ! ሰማያትን የሚሞላ፣ ምድርንም የሚሞላና በተጨማሪም ያሻህን ሁሉ የሚሞላ ምሥጋና ለአንተ ይሁን»

13. ቀጥሎም ለአላህ ፍጹም በመሆን (በኹሹ ዕ) በግንባሩ ተደፍቶ መሬት ላይ በመስገድ የመጀመሪያውን ሱጁድ ያደርጋል። ለሱጁድ ሲወርድም «አሏሁ አከበር» እያለ ይወርዳል። ሱጁድ የሚያደርገው ሰባት የአካል ክፍሎቹን ማለትም ግንባርና አፍንጫን፣ ሁለቱን መዳፎች፣ ሁለቱን ጉልበቶችና የእግሮቹን ጫፎች መሬት ላይ በማሳረፍ ሁለቱን ክንዶች ከወገቦቹ ከፊት በማድረግ ሲሆን ክንዶቹን መሬት ላይ አይዘረጋቸውም። የእግር ጣቶቹ ጫፍ ወደቅብላ አቅጣጫ ይሆናሉ።

14. በሱጁድ ወቅት ሦስት ጊዜ :- «سبحان ربي الأعلى»
«ሱብሐነ ረብብየል–አዕላ» (ከሁሉም በላይ ለዕላይ የሆነው ጌታዬ ጥራት ተገባው) ይላል። «سبحانك اللهم ربنا وبحمدك، اللهم اغفر لي»
«ሱብሓነከ አልሏሁምመ ረብበና ወብሐምድከ፣ አልሏሁምመ እግፊርሊ» የሚለውን ቢጨምር መልካም ነው።

15. ከዚያም «አሏሁ አከበር» እያለ ራሱን ከሱጁድ ቀና ያደርጋል።

16. ቀጥሎም በሁለቱ ሱጃዶች መካከል በግራ እግሩ ላይ ተቀምጦ የግራ እግሩን ጣቶች መሬት ላይ ይተከላል። የቀኝ እጁን በቀኝ ጉልበቱ ጫፍ ላይ በማሳረፍ ትንሿን ጣትና የቀለበት ጣት ጨብጦ ረዥሙን ጣትና አውራ ጣቱን በማጣመር አመልካች ጣቱን ቀስር በጸሎት ጊዜ ያንቀሳቅሰዋል። የግራ እጁ ጣቶች እንደተዘረጉ መዳፉን በጉልበቱ ልክ ጭኑ ላይ ያኖራል።

17. በሁለቱ ሱጁዶች መካከል በሚቀመጥበት ጊዜ:-
«رب اغفر لي
وارحمني واهدني وارزقني واجبرني وعافني».

«ረብብ እግፍርሊ፣ ወርሐምኒ፣ ወህድኒ፣ ወርዞቕኒ ወጅቡርኒ ወዓፍኒ» ይላል።

ትርጉሙ:- «ጌታ ሆይ! ማረኝ፣ እዘንልኝም፣ ምራኝም፣ ሲሳይም ለግሰኝ፣ ጠግነኝም አድነኝም »ማለት ነው።

18. ከዚያም ልቦናውን ለአላህ ፍጹም በማድረግ (በኹሹዕ) በቃልም ሆነ በድርጊት ከመጀመሪያው ጋር ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ «አሏሁ አክበር» ብሎ ሁለተኛ ሱጁድ ያደርጋል።

19. ቀጥሎም «አሏሁ አክበር» እያለ ከሁለተኛው ሱጁድ ቀና በማለት ተነስቶ ይቆምና በአንደበት በሚነበነበውም ሆነ በድርጊት የመክፈቻ ጸሎት ብቻ ሲቀር ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ ሁለተኛውን ረክዓ ይሰግዳል።

20. ከዚያም ሁለተኛውን ረክዓ ካበቃ በኋላ ልክ በሁለቱ ሱጁዶች መካከል በተቀመጠበት አኳኋን «አሏሁ አክበር» እያለ ይቀመጣል።

21. በዚህ የመቀመጫ ጊዜ የሚከተለውን «ተሸህሁድ» ያነባል:-

«التحيات

لله والصلوات والطيبات. السلام عليك أيها النبي ورحمة الله وبركاته. السلام علينا وعلى عباد الله الصالحين، أشهد أن لا إله إلا الله وأشهد أن محمدًا عبده ورسوله. اللهم صلِّ على محمد وعلى آل محمد، كما صليت على إبراهيم وعلى آل إبراهيم إنك حميد مجيد. وبارك على محمد وعلى آل محمد، كما باركت على إبراهيم وعلى آل إبراهيم إنك حميد مجيد. أعوذ بالله من عذاب جهنم، ومن عذاب القبر، ومن فتنة المحيا والمات، ومن فتنة المسيح الدجال».

«አትተሕይያቱ ሊልላህ ወስሶለዋቱ ወፐጠይይባቱ፣ አስሰላሙ ዐለይከ አይዩሀን–ነቢይዩ ወረሕመቱልሏህ ወበረካቱሁ፤ አስሰላሙ ዐለይና ወዐላ ዕባድልላህስ–ሷልሒን፣ አሽሀዱ አንላእላሀ እልላልሏህ ወአሽሀዱ አንነ ሙሐመደን ዐብዱሁ ወረሱሉሁ፤ አልሏሁምመ ሶልል ዐላ ሙሐመድን ወዐላ አል ሙሐመድን ከማ ሶልለይተ ዐላ ኢብራሂመ ወዐላ አል ኢብራሂም እንነከ ሐሚዱን መጂድ። ወባርከ ዐላ ሙሐመድን ወዐላ አል ሙሐመድን ከማ ባረክተ ዐላ ኢብራሂመ ወዐላ አል ኢብራሂመ እንነከ ሐሚዱን መጂድ። አዑዙ ብልላህ ምን ዐዛብ ጀሀንነም፣ ወምን ዐዛብል–ቐብር፣ ወምን ፍትነትል–መሕያ ወል–መማት፣ ወምን ፍትነትል–መሲሕ አድደጅጃል።»

ትርጉሙ:- « ክብር፣ ሶላቶችና መልካም ነገሮች ሁሉ የአሏህ ናቸው። አንተ ነቢዩ ሆይ! የአላህ ሰላም፣ እዝነቱና በረከቶቹ ለርስዎ ይሁን። ሰላም ለኛና ለደጋጉቹ የአሏህ አገልጋዮች ይሁን። ከአሏህ በስተቀር ሌላ አምላክ አለመኖሩን እመሰክራለሁ። አሏህ ሆይ! በአክብሮት የታጀበ እዝነትን ለኢብራሂምና ለቤተሰቦቻቸው ፦እንዳወረድክላቸው ለሙሐመድና ለቤተሰቦቻቸው አውርድላቸው፤ አንተ ምስጉንና ኃያሉ ነህና።ኢብራሂምና ቤተሰቦቻቸውን ብሩክ እንዳደረግካቸው ሁሉ ሙሐመድና ቤተሰቦቻቸውን ብሩክ አድርጋቸው። አንተ ምስጉኑና ኃያሉ ነህና። ከጀሀንነም ቅጣት ሥቃይ በአላህ እጠበቃለሁ። ከመቃብር ውስጥ ሥቃይም፤ ከሕይወትና ከሞት ፈተናዎች ሁሉም፤ ከሐሳዊው መሲሕ አድደጅጃልም።»

ከዚያም ከዚህ ዓለምና ከወዲያኛው ዓለም ሕይወት መልካም ነገሮች ውስጥ የወደደውን ነገር አላህን ይለምናል (ዱዓእ ያደርጋል)።

22. ቀጥሎም አንገቱን ወደ ቀኝ በማዞር «አስሰላሙ ዐለይኩም ወረሕመቱልሏህ» ይላል። ወደ ግራም እንደዚያው።

23. ሶላቱ ባለ ሦስት ረከዓ ወይም ባለ አራት ከሆነ በተሸህሁድ የመጀመሪያ ክፍል ላይ ማለት «...ዐብዱሁ ወረሱሉሁ...» በሚለው ላይ ያበቃል።

24. ከዚያ በመቀጠልም «አሏሁ አክበር» እያለና እጆቹን በትከሻዎቹ ትይዩ ከፍ እያደረገ ተነስቶ ይቆማል።

25. ቀጥሎም ቀሪውን የሶላቱን ረከዓ (ረከዓዎች) ሁለተኛውን ረከዓ በሰገደው ዓይነት ምንባቡን በፋቲሐ ብቻ ላይ በመወሰን ይሰግዳል።

26. ከዚያም ጉልበቶቹን ወደኋላ አጥፎ የቀኝ እግር ጣቶችን መሬት ላይ በመት ከል ያቆማል፤ የግራ እግሩን ከቀኝ ቅልጥሙ ሥር በማውጣት መቀመጫ ውን ከመሬት ያደላድላል። ሁለት መዳፎቹን በመጀመሪያው ‹ተሸህሁድ› ወቅት ባደረገው ዓይነት ከጉልበቶቹ ጫፍ በማስጠጋት ታፋው ላይ ያኖራል።

27. በዚህ አቀማመጥ ላይ ሙሉውን ‹ተሸህሁድ› ያነባል።

28. ከዚያም አንገቱን ወደ ቀኝ በማዞር «አስሰላሙ ዐለይኩም ወረሕመቱልሏህ» ይላል። በግራ በኩልም እንደዚያው።

## ሶላት ውስጥ የሚጠሉ ነገሮች

1. ሶላት ውስጥ በአንገትም ሆነ በዓይን ወደ ጐን ገልመጥ ማለት የተጠላ (መክሩህ) ሲሆን ወደ ሰማይ ማንጋጠጥ ደግሞ ሐራም ነው።
2. ሶላት ውስጥ እያሉ ከንቱ ነገር መሥራት (መጫወት) እና ለችግር ካልሆነ በስተቀር መንቀሳቀስ ይጠላል።
3. ሶላት ውስጥ ትኩረትና ሃሳብን የሚበታትን ከብደት ያለውና ትኩረትን የሚስብ ዓይነት ቡራቡሬ ነገር ማምጣት ወይም መያዝ ይጠላል።
4. ሶላት ውስጥ በእጅ ወገብ መያዝም ይጠላል።

## ሶላት የሚያበላሹ ነገሮች

1. ሆን ብሎ መናገር ትንሽ ቢሆን እንኳ ሶላት ያበላሻል።
2. ሰውነትን ሙሉ በሙሉ ከቁብላ አቅጣጫ ማዞርም ሶላት ያበላሻል።
3. በዓይነምድር መውጫ በኩል ከሆድ አየር ከወጣና ውዱእም ሆነ የገላ ትጥበ ትን ግዴታ የሚያስደርጉ ነገሮች ከተከሰቱ ሶላት ይበላሻል።
4. የግድ አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር ሶላት ውስጥ እያሉ ተከታታይ የሆኑ ብዙ ንቅናቄዎች ሶላት ያበላሻሉ።
5. ትንሽ ቢሆን እንኳ መሳቅ ሶላት ያበላሻል።

6. ሆን ብሎ እያወቁ ሩኩዕ፣ ሱጁድ፣ መቆምና መቀመጥን መጨመር ሶላት ያበላሻል።

7. ሆን ብሎ ከኢማም መቅደምም ሶላት ያበላሻል።

## የመርሳት ሱጁድን የሚገዙ ደንቦች

የመርሳት ጁጁድ (የመካካሻ ሱጁድ) ሦስት ምክንያቶች አሉት:-

- ጭማሪ
- ጉድለት
- ጥርጣሬ

### ጭማሪ (ዝያዳህ)

ለምሳሌ ያህል አንድ ሰው በሶላቱ ውስጥ በአንድ ረከዓ ሁለት ሩኩዕ በማድረግ ወይም ሦስት ጊዜ ሱጁድ በማድረግ ወይም ደግሞ ባለ አራት ረከዓ እየሰገደ ለአምስተኛ ረከዓ ተነስቶ በመቆም ሲያስታውስ ተመልሶ መቀመጥን የመሳሰሉ ናቸው። በነኚህ ምክንያቶች የማካካሻ ሱጁድ የሚደረገው ከሰላምታ በኋላ ነው። ይህም ማለት ‹ተሸህሁድ› ከተቀራና ሰላምታ ከተባለ በኋላ ሁለት ሱጁዶች ማድረግ ማለት ነው። ነቢዩ (ሰዐወ) አምስት ረከዓ በሰገዱ ጊዜ ከሰላምታ በኋላ ሲያስታውሷቸው ከሰላምታ በኋላ ሱጁድ በመውረድ ያደረጉት እንዲህ ነበር።

ነቢዩ (ሰዐወ) እዚህ ላይ ከሰላምታ በኋላ ሱጁድ የወረዱት መርሳታቸውን ከሰላምታ በኋላ እንጂ ስላላወቁ ነው አይባልም። ነገሩ እንደዚያ ነው፤ ነገር ግን እኛ የምንለው:- ደንቡ እሳቸው ካደረጉት የሚለይ ቢሆን ኖሮ ሶላቱን በሰላምታ ከማጠቃለላችሁ በፊት ተጨማሪ ነገር ማድረጋችሁን ካወቃችሁ ከሰላምታ በፊት የማካካሻ ሱጁድ አድርጉ ባሏቸው ነበር ነው። ነገሩን በነበረበት ሁኔታ ሲያጸድቁም ለተጨማሪ ነገር የሚደረገው የማካካሻ ሱጁድ ከሰላምታ በኋላ መሆኑ ታወቀ።

ነቢዩ(ሰዐወ) በዙህር ወይም ዐስር ሶላት ከሁለተኛው ረከዓ በኋላ በሰላምታ ሲያጠቃልሉ ሰሓባ አስታወሷቸው ሶላቱን አሟልተው ከሰገዱ በኋላ ሰላምታ

ብለው ሁለት ሱጁድ መውረዳቸው ይህንኑ ያመለክታል። ይኸውም በሶላት ውስጥ እያሉ ያለ ቦታው ሰላምታ ማለት ተጨማሪ ነገር(ዝያዳህ) በመሆኑ ነቢዩ (ሰዐወ) ይህንኑ ለማካካስ ከሰላምታ በኋላ ሁለት ሱጁድ ወርደዋል። ይህ አቋም ነቢያዊውን ፈለግ መሠረት ያደረገ ከመሆኑም በተጨማሪ ሕሊናዊውን ግንዛቤም የተመረኮዘ ነው። በሶላት ውስጥ አንድ ነገር ከተጨመረ የመካካሻ ሱጁድ የሚደረገው ከሰላምታ በፊት ነው ካልን በሶላቱ ውስጥ ሁለት ተጨማሪ ነገሮች ተከሰቱ ማለት ነው። ከሰላምታ በኋላ ሱጁድ ይደረጋል ካልን ግን በሶላቱ ውስጥ የተከሰተው በዝንጋታ ተጨማሪ ነገር ብቻ ነው ማለት ነውና።

## ጉድለት (ነቅስ)

ተረስቶ ከሶላት ውስጥ አንድ ነገር ከተጓደለ ለማካካሻ የሚደረገው የመርሳት ሱጁድ ከሰላምታ በፊት ነው። ለምሳሌ ያህል ሰጋጁ የመጀመሪያውን ተሸህሁድ ሳያነብ ረስቶ ተነስቶ ቢቆም፣ ወይም በሱጁድ ላይ ‹ሱብሓነ ረብብየል–አዕላ› ማለትን ቢዘነጋ፣ ወይም ሩኩዕ ላይ ‹ሱብሓነ ረብብየል–ዐዚም› ማለትን ቢረሳ ይህን ግዴታ (ዋጅብ) በመተው ሶላቱ በመጉደሉ ለማካካሻ ሱጁድ የሚደረገው ከሰላምታ በፊት ነው። ከሶላቱ ከመለያየቱ በፊት የዘነጋውን ነገር በመርሳት ሱጁድ ማካካሱ ጥበብን የተመረኮዘ ይሆናል።

‹ነቢዩ (ሰዐወ) የዙህርን ሶላት መርተው እያሰገዷቸው ከሁለተኛው ረከዓ በኋላ ሳይቀመጡ በመነሳት ሶላቱን ካሟሉ ሰው ሶላቱን በሰላምታ ያገባድዳሉ ብሎ ሲጠባበቅ አሏሁ አክበር ብለው ሁለት ሱጁድ በመውረድ ከዚያ በኋላ ሰላቱን በሰላምታ አበቁ› የሚለው የዐብዱልኣህ ብን ቡሐይናህ ሐዲሥ ይህንኑ ያመለክታል።

## ጥርጣሬ (ሸክክ)

ሶላቱ ውስጥ ተጨማሪ ነገር ወይም ጉድለት አደረስኩ አላደረስኩም ብሎ ሰጋጁ ሦስት ይሁን አራት ረከዓ እንደሰገደ ሲጠራጠር ጥርጣሬው በሁለት መንገድ ይታያል።

አንደኛው ገጽታ:- ከመጨመር ወይም ከማጉደል ጥርጣሬ አንደኛው አመዝኖ ከታየው በአመዛኙ ጥርጣሬ ላይ በመመርኮዝ ሶላቱን አሟልቶ ለማካካ

ሻው የመርሳት ሱጁድ ከሰላምታ በኋላ ይወርዳል። በእብን መስዑድ (ረዐ) ሐዲሥ ውስጥ በተመለከተው መሠረት ማለት ነው:- «አንደኛችሁ በሶላቱ ውስጥ ጥርጣሬ ካደረበት ትክክለኛውንና ይሆናል የሚለውን በመውሰድ በዚያ መሠረት ላይ ሶላቱን አሟልቶ በሰላምታ ካበቃ በኋላ ሁለት ሱጁድ ያድርግ...»። ነቢዩ (ሰዐወ) እንዲህ ወይም የዚህ ይዘት ያለው ነገር ተናግረዋል።

ሁለተኛው ገጽታ:- ሶላቱ ውስጥ ተጨማሪ ነገር ወይም ጉድለት የመከሰት አለመከሰት ጥርጣሬ አድሮበት ግን ደግሞ አንደኛው ጥርጣሬ ከሌላው አመዝኖ ካልታየው ትክክለኛ ነው ብሎ በሚያምነው በአነስተኛው ላይ ተመሥርቶ ሶላቱን በማሟላት ከሰላምታ በፊት የማካካሻ ሱጁድ ያደር ጋል። በዚህ መልኩ ነው ሱንናው ከነቢዩ (ሰዐወ) የተላለፈው።

ሶላትን ከሚያበላሹ ነገሮች ውስጥ በተጨማሪ ለቀጣዩ ጥያቄ በተሰጠው ምላሽ ውስጥ እንደተመለከተው ገላን በውስጡ በሚያሳይ ስስ ልብስ መስገድ አንዱ ነው:-

ክቡር ሸይኽ ሙሐመድ ብን ሷልሕ አል–ዑሠይሚን፤ አስሰላሙ ዐለይኩም ወረሕመቱልሏህ ወበረካቱሁ፣ ለዚህ ጥያቄ መልስ እንደሚሰጡኝ ተስፋ አደርጋለሁ:-

ብዙ ሰዎች ከሥር ያለውን ገላቸውን በሚያሳዩ ቀላልና ስስ ልብሶች ይሰግዳሉ፤ በነዚህ ልብሶች ሥር ከጭን አጋማሽ የማያልፉ አጫጭር ቁምጣዎች ይለብሱና ቀሪው የጭናቸው ግማሽ ክፍል ከልብሶቹ ውስጥ አልፎ ይታያል። የነኚህ ሰዎች ሶላት እንዴት ይታያል?

በአላህ ስም፣ እጅግ በጣም ርህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው፤ ወዐለይኩም አስሰላም መረሕመቱልሏህ ወበረካቱሁ

የነዚህ ሰዎች ሶላት የሚታየው ከአጫጭር ቁምጣዎች በስተቀር ያለ ልብስ እንደ ሰገደ ሰው ሶላት ነው። ገላን የሚያሳዩ ስስ ልብሶች አካልን የማይሸፍኑ በመሆናቸው መኖራቸውና አለመኖራቸው እኩል ነው። በዚህ መሠረትም ከሊቃውንት (ዓሊሞች) ሁለት አቋሞች ይበልጥ ትክክለኛ (አስሕ) በሆነው

አቋም ሰላታቸው ብቁ (ሶሒሕ) አይደለም። በኢማም አሕመድ(ረዐ) መዝሀብ በስፋት የታወቀ (መሽሁር) አቋምም ይኸው ነው። ይህም ወንድ ሰጋጅ ከገላው በእምብርትና በጉልበት መካከል ያለውን ክፍል ሙሉ በሙሉ መሸፈን ግዴታ (ዋጅብ) በመሆኑ ሲሆን ቀጥሎ የሰፈረው የአላህ (ሱወ) ቃል ተፈጻሚነት የሚኖረው በአነስተኛው በዚህ ስለሆነ ነው:-

﴿يا بني آدم خذوا زينتكم عند كل مسجد﴾

«የአዳም ልጆች ሆይ! (ኀፍረተ ገላችሁን የሚሸፍኑትን) ጌጦቻችሁን በመስገጃው ሁሉ ዘንድ (በሶላትና በጠዋፍ ጊዜ) ያዙ!..»[1]

ከሚከተሉት ሁለት ነገሮች ውስጥ አንዱ ግዴታ ይሆንባቸዋል:- ወይም በእምብርትና በጉልበቶች መካከል ያለውን የሰውነት ክፍል የሚሸፍኑ ሱሪዎችን መልበስ ወይ ደግሞ በነዚያ አጫጭር ቁምጣዎች ላይ ገላን የማያሳይ ወፈር ያለ ልብስ ደርበው መልበስ ነው። በጥያቄው ውስጥ የተጠቀሰው ይህ ድርጊት ስሕተትና ከባድ ነውና በድርጊታቸው ተጸጽተው ወደ አላህ (ሱወ) መመለስ (ተውበት ማድረግ) እና በሶላቶቻቸው ውስጥ መሸፈን የሚገባቸውን አሟልተው ለመሸፈን መትጋት ይኖርባቸዋል። እኛንና ሙስሊም ወንድሞቻችንን ወደሚወደውና ወደሚቀበለው ነገር እንዲመራንና ለዚህም ይገጥመን ዘንድ አላህን (ሱወ) እንለምነዋለን፣ እርሱ ቸርና ለጋስ ነውና።

በረመዷን 5 ቀን 1408 ዓመተ ሀጅራ

ሙሐመድ አስ–ሷልሕ አል–ዑሠይሚን ጻፈው።

---

1 አል–አዕራፍ (7):31

# የመርሳት ሱጁድን የሚገዙ ደንቦች ማጠቃለያ

| ጉዳዩ (ነገሩ) | አኳኋኑ | የሱጁዱ ጊዜ |
| --- | --- | --- |
| ሶላቱ ከመሟላቱ በፊት በመርሳት ሰላምታ ማለት:- ሰጋጁ ሶላቱን ሳያ ሟላ ረስቶ ሰላምታ ካለ | ብዙ ጊዜ ካለፈ በኋላ ያስታወሰ ከሆነ ሶላቱን እንደገና እንደ አዲስ ይጀምራል። ከአጭር ጊዜ በኋላ እንደ አምስት ደቂቃ ባለ ጊዜ ውስጥ የረሳውን ነገር ካስታወሰ ሶላቱን ያሟላና ሰላምታ ይላል። | ከሰላምታ በኋላ ሁለት የመርሳት ሱጁዶች ይወርድና ለሁለተኛ ጊዜ ሠላምታ ይላል |
| በሶላት ውስጥ ተጨማሪ (ዝያዳህ) ሲከሰት:- ሰጋጁ ሶላቱ ላይ በመቆም በመቀ መጥ በሩኩዕ ወይም በሱጁድ ላይ ከጨመረ | ተጨማሪው ከተከሰተ በኋላ ካስታወሰ የመርሳት ሱጁድ መውረድ አለበት። ጭማሪው በመከሰት ላይ እያለ ካስታወሰ ግን ከጭማሪው ወዲያውኑ የመታቀብ ግዴታ አለበት። | በመርሳት ከሰላምታ በኋላ ሁለት ሱጁድ ወርዶ ከዚያ በኋላ እንደገና ሰላምታ ይላል። |
| ከሶላት አበይት ክፍሎች (አርካን) አንዱን መተው ሲከሰት:- | በቀጣዩ ረከዓ ላይ ረስቶት ወደ ነበረው ቦታ ደርሶ ከሆነ ሩክኑን የረሳበት ቀዳሚው ረከዓ ውድቅ ሆና ቀጣዩ ረከዓ በርሱ ፈንታ ይቆጠራል። በቀጣዩ ረከዓ ላይ ረስቶት ወደ ነበረው ቦታ ላይ ገና ያልደረሰ ከሆነ ግን የረሳውን ተመልሶ ማሟላትና ከዚያ በኋላ ያለውን በተራው መሠረት ማከናወን ይኖርበታል | በሁለቱም ሁኔታዎች የማካካሻ ሱጁድ ማድረግ ግዴታ የሚሆንበት ሲሆን ጊዜውም ከሠላምታ በኋላ ነው |
| በሶላት ውስጥ የመጠራጠር ሁኔታ ሲከሰት:- በሰገዳቸው ረከዓዎች ቁጥር ሁለት ይሁን ወይስ ሦስት ሰገድኩ ብሎ ሲጠራጠርና ነገሩ ከሁለቱ አንዱ ሲሆን | በመጀመሪያው ሁኔታ:- ከሁለቱ አንዱን ይበልጥ አመዛኝ ሆኖ ሲያገኝ አመዛኝ በሆነው ላይ ተመርኩዞ ሶላቱን በማሟላት በሠላምታ ያጠቃልላል። በሁለተኛው ሁኔታ:- ከሁለቱ ጥርጣሬዎች አንዱንም አመዛኝ ሆኖ ካላገኘው በእርግጠኛው ላይ ማለትም በአነስተኛው ቁጥር ላይ ተመሥርቶ ሶላቱን በማሟላት በሠላምታ ያጠናቅቃል። | በመጀመሪያው ሁኔታ የመርሳት ሱጁድን ከሠላምታ በኋላ ያደርጋል። በሁለተኛው ሁኔታ የመርሳት ሱጁዱን ከሠላምታ በፊት ያደረጋል። |

| ጉዳዩ (ነገሩ) | አኳኋኑ | የሱጁዱ ጊዜ |
|---|---|---|
| የመጀመሪያው ተሸሁድ (አትተሒይያቱ) ተረስቶ ሲቀር ሌሎች የሶላት ግዴታዎችን (ዋጅባት) የሚገዛ ደንብ የመጀመሪያውን ተሸህሁድ የሚገዛ ሕግ ነው። | 1. ቀጥ ብሎ ከቆመ በኋላ እንጂ መርሳቱን ካላስታወሰ ሶላቱን ይቀጥላል እንጂ ለተሸህሁድ ተመልሶ አይቀመጥም። 2. ከተነሳና ቀጥ ብሎ ከመቆሙ በፊት መርሳቱን ካስታወሰ ግን ተመልሶ በመቀመጥ ተሸህሁድ አድርጐ ሶላቱን ያሟላል። 3. ታፋውን ከቅልጥሞቹ አላቆ ከመጨረሱ በፊት ካስታወሰ እንደገና ተመቻችቶ በመቀመጥ ተሸህሁድ በማድረግ ሶላቱን ያሟላል። በዚህ ሁኔታ ምንም የቀነሰውም ሆነ የጨመረው ነገር ባለመኖሩ የመርሳት ሱጁድ አይወርድም። | ከሠላምታ በፊት የመርሳት ሱጁድ ይወርዳል። |

1. ሰጋጁ ሶላቱን ከማሟላቱ በፊት ሆን ብሎ እያወቀ ሠላምታ ካደረገ ሶላቱ ይበላሻል።

2. ሰጋጁ ሶላቱ ውስጥ መቆም፣ መቀመጥ፣ ሩኩዕ ወይም ሱጁድ እያወቀ ሆን ብሎ ከጨመረ ሶላቱ ይበላሻል።

3. ከሶላት ማዕዘናት (አርካን) ውስጥ አንዱን ማዕዘን ከተወ፣ የተተወው ማዕዘን ተክቢረቱል–እሕራም (የሶላት መግቢያ ትክቢራ–አሏሁ አክበር) ከሆነ አውቆም ሆነ ረስቶ ቢተወው ሶላቱ ከመጀመሪያው ያልተመሠረተ በመሆኑ ፋርሽ ነው፤ የተተወው ማዕዘን ከተክቢረቱል–እሕራም ሌላ ከሆነና ሆን ብሎ የተወው ከሆነ ሶላቱ ፋርሽ ነው።

4. ከሶላት ዋጅቦች ውስጥ አንዱን ሆን ብሎ ከተወ ሶላቱ ፋርሽ ይሆናል።

5. የመርሳት ሱጁድ ከሠላምታ በኋላ ተደርጐ ከሆነ ለሁለተኛ ጊዜ ሠላምታ ማለት የግድ ነው።

# የቁርአን ምንባብ ሱጁድ (ሱጁድ አት–ትላዋ)

የምንባብ ሱጁድ ምክንያት አንድ ሰው ቁርአን ሲያነብ ወይም ሲነበብ ሲያደምጥ ሰጅዳህ ባለበት አንቀጽ ሲያልፍ ነው። ቅዱስ ቁርአን ውስጥ ሱጁድ የሚወረድባቸው ሥፍራዎች የታወቁና በመጻሕፍቱ ሕዳጎች ላይ ምልክት የተደረጉባቸው ናቸው። አንድ ሰው በአንዱ ሰጅዳ ሲያልፍ ለአላህ (ሱወ) ሱጁድ መውረድ አጥብቆ ይፈለግበታል። እንዲያውም አንዳንድ ዓሊሞች የቁርአን ምንባብ ሱጁድ ግዴታ (ዋጅብ) ነው ብለዋል። ትክክለኛው (ሶሒሑ) አቋም ግን ዋጅብ አይደለም የሚለው ነው። የምእመናን አዛዥ የሆኑት ዑመር ብን አል–ኸጧብ (ረዐ) አንድ ቀን የጁሙዓ ኹጥባ አድርገው በሱረት አን–ነሕል ውስጥ ያለውን የሰጅዳ አንቀጽ አንብበው ሱጁድ ወረዱ፤ ከዚያም በሌላው ጁሙዓ አንቀጹን አንብበው ሳይወርዱ ቀሩና ‹አላህ ብንፈልግ እንጂ (የትላዋ) ሱጁዱን ግዴታ አላደረገብንም› ብለዋል። ይህም ማለት ከፈለግን ብቻ እናደርጋለን ማለት ነው። ብንፈልግ እንጂ ማለት ስለፈለግነው ግዴታ አደረገብን ማለት አይደለም፤ የአላህ የግዴታ ትእዛዛት በኛ ፍላጎት ላይ አይመረኮዙምና። ዑመር ይህን ያደረጉት ሰሓባ ባሉበት ቦታ ሲሆን መጥፎ የሆነውን ነገር ለመቃወም ወደ ኋላ ካለማለታቸው ጋር ከሰሓባ አንድም ሰው ድርጊቱን አልተቃወመም። በዚህ ታላቅ ትዕይንት ላይ በቀጥተኛው ኸሊፋ በዑመር ብን አል–ኸጧብ (ረዐ) የተፈጸመውን ጉዳይ ሰሓቦች ማጽደቃቸው የትላዋ ሱጁድ በሶላት ውስጥም ሆነ ከሶላት ውጭ ግዴታ (ዋጅብ) አይደለም የሚለው አቋም ትክክለኛ (ሰሒሕ) መሆኑን ያመለክታል።

## የትላዋ ሱጁድ አኳኋን

የሱጁዱን አደራረግ በተመለከተ አኳሁ አክበር ተብሎ ልክ እንደ ሶላት ሱጁድ በሰባቱ የአካል ክፍሎች ሱጁድ በመውረድ የተለመደውን (ከፍ ሲል የተጠቀሰውን) የሱጁድ ጸሎት ይልና የሚከተለው የታወቀ ዱዓእ ያደርጋል:-

«اللهم لك سجدت وبك

آمنت وعليك توكلت. سجد وجهي لله الذي خلقه

وصوّره وشق سمعه وبصره، بحوله وقوته. اللهم

اكتب لي بها اجرًا، وارفع عني بها وزرًا واجعلها لي

عندك ذخرًا، وتقبلها مني كما تقبلتها من عبدك داود».

«አልሏሁምመ ለከ ሰጀድቱ ወብከ አመንቱ ወዐለይከ ተወክከልቱ። ሰጀደ ወጅሂ ልልላህ–ለዚ ኸለቀሁ፣ ወሰዉወረሁ፣ ወሸቐቐ ሰምዐሁ፣ ወበሰረሁ ብሐውልሂ ወቁዉወትህ። አልሏሁምመ እክቱብሊ ብሃ አጅረን፣ ወርፈዕ ዐንኒ ብሃ ውዝረን፣ ወጅዐልሃሊ ዕንደከ ዙኽረን፣ ውተቐብበልሃ ምንኒ ከማ ተቐብበልተሃ ምን ዐብድከ ዳውድ»።

ትርጉሙ :- «አላህ ሆይ! ላንተ ሰገድኩ! ባንተም አመንኩ! ባንተ ላይም ተማመንኩ! ፊቴ ለዚያ በጥበቡና በኃይሉ ለፈጠረው፣ ለቀረጸው፣ መስሚያና ማያውንም ለቀደደለት (ለፈጠረለት) አላህ ሰገደ። አላህ ሆይ! በርሱ (በሱጁዱ) ምንዳ ፃፍልኝ! በርሱም ኃጢአትን አራግፍልኝ! አንተ ዘንድም ተቀማጭ የሚሆን አድርገልኝም! ከአገልጋይህ ከዳውድ እንደተቀበልከው ሁሉ ከኔም ተቀበለው።» ማለት ነው። ከዚያም ያለ ተክቢራና ያለ ሠላምታ ከሱጁዱ ቀና ይላል።

በሶላት ላይ እያለ የትላዋ ሱጁድ ካደረገ ግን ሱጁድ ሲወርድ አሏሁ አክበር ይላል፤ ቀና ሲልም አሏሁ አክበር ይላል። ይኸውም የነቢዩን (ሰዐወ) የአሰጋገድ ሁኔታ የገለጹ ዘጋቢዎች ሁሉ ባጐንበሱና ቀና ባሉ ቁጥር አሏሁ አክበር ይሉ እንደነበረ ስለገለጹ ነው።

ነቢዩ (ሰዐወ) በዕሻእ ሶላት የአል–እንሽቃቕን ምዕራፍ አንብበው የትላዋ ሱጁድ መውረዳቸው በአቡ ሁረይራ ሐዲስ እንደተረጋገጠው ሁሉ ሰላት ውስጥ የትላዋ ሱጁድ ይወርዱ ነበር።

## ሶላት የተወን ሰው የሚመለከት ሕግ

ጥያቄ–አንድ ሰው ቤተሰቦቹን እንዲሰግዱ አዟቸው ካልሰሙት ምን ያደርጋል? ከነሱ ተቀላቅሎ አብሯቸው ይኖራል ወይስ ከቤቱ ትቶ ይወጣል?

መልስ– እነኚህ ቤተሰቦች ጭራሽ የማይሰግዱ ከሆኑ ከሐዲዎች (ኩፍፋር)፣ ተቀልባሾች (ሙርተድ) እና ከእስላም ጐራ የወጡ ስለሆኑ ከነርሱ ጋር አብሮ መኖር አይፈቀድም። ይሁን እንጂ እንዲሰግዱ ጥሪ ማድረግ መጐትጐትና ደጋግሞ ማሳሰብ ግዴታ ይሆንበታል። አላህ ወደ ቅኑ መንገድ

ይመራቸው ይሆናልና። ይህም ሶላትን የተወ ሰው (ታሪክ አስሶላት) -አላህ ይጠብቀንና- በቁርአን በሱንና፣ በሰሓባ ቃልና በትክክለኛ አእምሮ ማስረጃ ካፊር በመሆኑ ነው።

- የቁርአንን ማስረጃ በተመለከተ አላህ (ሱወ) ስለ ሙሽሪኮች የተናገረው የሚከተለው ቃሉ ነው:-

﴿فإن تابوا وأقاموا الصلاة وآتوا الزكاة فإخوانكم في الدين﴾

«ቢጸጸቱም፣ ሶላትንም ቢሰግዱ፣ ዘካንም ቢሰጡ፣ የሃይማኖት ወንድሞቻችሁ ናቸው፤...»[1]

ከአንቀጹ መገንዘብ የሚቻለው ያንን ካላደረጉ ወንድሞቻችን አለመሆናቸው ነው። ሃይማኖታዊ ወንድማማችነት ደግሞ የቱን ያህልም ከባድ ቢሆን በኃጢአቶች ምክንያት ውድቅ አይደረግም፤ ከእስላም ጉራ በመውጣት እንጂ።

¤ የሱንናን ማስረጃ በተመለከተ ቀጥሎ ያለው የነቢዩ (ሰዐወ) ቃል ነው:-

«بين الرجل وبين الكفر والشرك ترك الصلاة» أخرجه مسلم.

«በአንድ ሰውና በክሕደት (ኩፍር)፣ በማጋራት (ሽርክ) መካከል ያለው (መለያ) ሶላት መተው ነው።»[2]

«العهد الذي بيننا وبينهم الصلاة فمَن تَركها فقد كفر».

«በኛና በነሱ (በከሐዲዎቹ) መካከል ያለው (የመለያ) ኪዳን ሶላት ነው፤ (ሶላትን) የተወው ሰው በእርግጥ ከሐዲ ሆኗል።»

የሚለውና ከቡረይዳህ (ረዐ) በተዘገበው ሐዲሥ ውስጥ የተመለከተው ነው።

¤ የሰሐባ ቃሎችን በተመለከተ ደግሞ የምእመናን አዛዥ የሆኑት ዑመር እብን አል-ኽጧብ(ረዐ) እንዲህ ብለዋል:-

لاحظَّ في الإســلام لمن ترك الصــلاة

«ሶላት የተወ ሰው እስላም ውስጥ (ይብዛም ይነስ) ዕጣ ፈንታ የለውም።»

---

1 አል-ተውባህ (9):11

2 ሙስሊም ያጠናቀሩት ሐዲሥ

¤ ዐብዱልሏህ ብን ሸቂቅም እንዲህ ብለዋል:-

كان أصحاب النبي ، ﷺ، لا يرون شيئًا من الأعمال تركه كفر غير الصلاة.

«የነቢዩ (ሰዐወ) ሰሓቦች ከሥራዎች ሁሉ መተው ኩፍር የሆነ ከሶላት በስተቀር ሌላ ምንም ነገር አለ ብለው አያስቡም ነበር።»

የትክክለኛ አእምሮን ሕሊናዊ ማስረጃ በተመለከተ ደግሞ:- የሰናፍጭ ፍሬ ያህል እምነት እንኳ እልቡ ውስጥ ያለውና የሶላትን ታላቅነትና አላህ ለሶላት የሰጠውን ትኩረት የሚያውቅ ሰው ሶላትን በመተው ላይ ይተጋል ተብሎ ይታሰ ባልን? ይህ ሊሆን የሚችል አይደለም። ሶላት የተወ ሰው ከሓዲ (ካፊር) አይሆ ንም የሚለው ወገን የሚያቀርባቸውን ማስረጃዎች መርምሬ ከሚከተሉት አም ስት ሁኔታዎች የማይወጡ ሆነው አግኝቻለሁ:-

1. ወይ ከነጭራሹ ለዚህ ማስረጃ አይደሉም።
2. ወይ ደግሞ ሶላትን ለመተው ሊውል በማይችል አገላለጽ የታጠሩና የተገደቡ ናቸው።
3. ወይ ደግሞ ሶላቱን በመተው የሚታለፍ መሆኑን በሚያመለክት ሁኔታ የተወሰኑ ናቸው።
4. ወይ ደግሞ አጠቃላይ (ዓምም) ሆነው ሶላት የተወ ሰው ካፊር መሆኑን በሚናገሩ ሐዲሦች ልዩ (ኻስ) የሚደረጉ ናቸው።
5. ወይም ደግሞ ደካማ (ዷዒፍ) ሆነው ትክክለኛ (ሰሒሕ) በሆኑ ሐዲሦች ፊት መጽናት የማይችሉ ናቸው።

በእስላማዊ የሕግ አንቀጾች (ኑሱስ) ውስጥ ሶላት የተወ ሰው አማኝ ነው፣ ወይም ጀነት ይገባል፣ ወይም ከእሳት ይድናል እና ይህን የመሳሰለ ነገር የሚያመ ለክት አንቀጽ የለም። ስለዚህም ሶላት የተወ ሰው (ታሪክ አስሰላት) ላይ የተደነገ ገውን የከሐዲነት (የኩፍር) ውሳኔ ጸጋን መካድና ማስተባበል ወይም ከክሕደት ያነሰ ክሕደት (ኩፍሩን ዱነ ኩፍር) ነው ወደሚል ንጽጽራዊ ትርጓሜ (ተእዊል) እንድንሄድ የሚያደርገን አንዳች ነገር የለም። ሶላት የተወ ሰው ከእስላም የተቀ ለበሰ ከሐዲ (ሙርተድ) መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ ክሕደቱ በተቀልባሾች ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ ድንጋጌዎችን ያስከትልበታል። ከነዚህም መካከል:-

አንደኛ– ለርሱ ልጅ መዳር ትክክለኛ አይሆንም። የጋብቻ ውል ተፈጽሞለት እርሱ የማይሰግድ ከሆነ ውሉ (ንካህ) ውድቅ ነው። ሚስቲቱም ለርሱ ሐላል አትሆንለትም።

● ይህም አላህ (ሱወ) ሴት ስደተኞችን (ሙሃጅራትን) አስመልክቶ የተናገረው የሚከተለውን የቁርኣን አንቀጽ ነው:-

﴿فإن علمتموهن مؤمنات فلا ترجعوهن
إلى الكفار، لا هن حِلّ لهم ولا هم يحلون لهن﴾

«አማኞች መሆናቸውን ብታውቁ ወደ ከሐዲዎቹ አትመልሱአቸው። እነርሱ (ሴቶቹ) ለነርሱ የተፈቀዱ አ ይደለምና።...»[1]

ሁለተኛ– የጋብቻ ውሉ ከተደፈጸመለት በኋላ ሶላት የተወ ከሆነ ጋብቻው ውድቅ ሆኖ ሚስቲቱም ለርሱ አትፈቀድለትም። ይህም ከላይ በጠቀስነው አንቀጽ መሠረትና መሆን ያለበት ከሚስቲቱ ጋር የግብረሥጋ ግን ኙነት ከመፈጸሙ በፊት ወይም በኋላ መሆኑን በተመለከተ በሊቃውንት ዘንድ በሚታወቀው ዝርዝር ማብራሪያ ላይ በመመርኮዝ ነው።

ሦስተኛ – ይህ የማይሰግድ ሰው ያረደው ሥጋም አይበላም። ለምን? ሥጋው ሐራም በመሆኑ ነው። አንድ አይሁዳዊና ወይም ክርስቲያን ሰው ያረደው ሥጋ መብላት ለኛ ይፈቀዳል። የማይሰግድ ሰው ያረደው ግን –አላህ ከዚህ ይጠብቀንና–ከአይሁዳዊ ወይም ከክርስቲያን እርድ ይበልጥ የተጠላና የሚጠየፍ ይሆናል ማለት ነው።

አራተኛ–ወደ መካ ወይም ወደ ክልሉ (ሐረሙ) መግባት አይፈቀድለትም። ይህም ቀጥሎ ባለው የአላህ (ሱወ) ቃል መሠረት ነው:-

﴿يا أيها الذين آمنوا إنما المشركون نجس
فلا يقربوا المسجد الحرام بعد عامهم هذا﴾.

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አጋሪዎች፣ እርኩሶች ብቻ ናቸው፤ ከዚህ ዓመታቸው (ዘጠነኛ ዓመተ ሀጅራ) በኋላ፣ የተከበረውን (የመካ)መስጊድ አይቅረቡ፤...»[2]

1 አል–ሙምተሕናህ 60:10

2 አል–ተውባህ (9):28

አምስተኛ–አንድ የሥጋ ዘመዱ ቢሞት ከንብረቱ የውርስ ድርሻ የማግኘት መብት አይኖረውም። አንድ ሰው የማይሰግድ ልጅ ትቶ (አባቱ የሚሰ ግድ ሙስሊም ሆኖ ልጅ የማይሰግድ ሆኖ) ቢሞት፣ ከዚህ ከማይሰግደው የአብራኩ ልጅና (የሚሰግድ ከሆነ) የወንድሙ ልጅ መካከል የትኛቸው ነው ሟቹን የሚወርሰው? የገዛ ልጁ ሳይሆን የሩቅ ዘመዱ የሆነው የወን ድሙ ልጅ (የልጁ የአጐት ልጅ) ነው የሚወርሰው። ይህም ከኡሳማ (ረዐ) በተላለፈው ሐዲሥ ውስጥ ነቢዩ (ሰዐወ):-

«لا يرث المسلم الكافر ولا الكـافر المسلم»

«ሙስሊሙ ካፊሩን፣ ካፊሩም ሙስሊሙን አይወርስም።»[1] በማለት በተናገሩትና:-

«ألحقوا الفرائض بأهلها فما بقي فلأولى رجل ذكر» متفق عليه،

«የውርስ ድርሻዎችን ለባለቤቱ አድርሱ፤ የተረፈውን ይበልጥ የተገባው ለሆነው ወንድ (የሩቅ ወራሽ) አድርጉ።»[2] በሚለው ቃላቸው መሠረትነው። ይህ በሁሉም ወራሾች ላይ ተግባራዊ የሚሆን ምሣሌ ነው።

ስድስተኛ–ከሞተም ሬሳው አይታጠብም፣ አይከፈንም፣ አይሰገድበትም፣ በሙስሊሞች መካነ–መቃብርም አይቀበርም። ታድያ ምን እናደርገ ዋለን? ወደ በረሃ እንወስደውና ጉድጓድ ቆፍረንለት በለበሰው ልብሱ እንቀብረዋለን። ከበሬታ የለውምና። በዚህ መሠረት አንድ ሰው ሌላ ሰው እርሱ ዘንድ ከሞተና ሟቹ የማይሰግድ መሆኑን የሚያውቅ ከሆነ በአስከሬኑ ላይ ሙስሊሞች እንዲሰግዱ ለሙስሊሞች ማቅረብ አይፈቀድም።

ሰባተኛ– በትንሣኤ (ቕያማ) ቀን ከፊርዐን ከሃማን ከቓሩንና ከኡበይ እብን ኸለፍ ጋር–ከዚህ አላህ ይጠብቀንና–ከክሕደት (ኩፍር) መሪዎች ጋር ይቀሰቀሳል። ጀነት አይገባም፣ ከዘመዶቹ ውስጥ ማንም ሰው አላህ ይቅር እንዲለውና ምሕረት እንዲያደርግለት እንዲጸልይለት አይፈቀድም፣ ቀጥሎ ባለው የአላህ ቃል መሠረት በከሐዲነቱ ምሕረት የማይገባው ነውና:-

---

1 ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት

2 ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት

﴿ما كان للنبي والذين آمنوا أن يستغفروا للمشركين ولو كانوا أولي قربى من بعد ما تبين لهم أنهم أصحاب الجحيم﴾.

«ለነቢዩና ለነዚያ ላመኑት፥ ለአጋሪዎቹ፥ የዝምድና ባለቤቶች ቢኾኑም እንኳ፥ እነሱ (ከሓዲዎቹ) የእሳት ጓዶች መኾናቸው ከተገለጸላቸው በኋላ ምሕረትን ሊለምኑ የሚገባ አልነበረም።»[1]

ወንድሞቼ! ነገሩ በጣም አደገኛ ነው...አንዳንድ ሰዎች ግን–በጣም ያሳዝናል–በዚህ ጉዳይ ላይ ችላ ይላሉ! የማይሰግድ ሰው እቤታቸው ውስጥ እንዲቆይ ያደርጋሉ። ይህ ግን የማይፈቀድ ነው..። ከሁሉም በላይ የሚያውቅ አላህ ነው። ከአከብሮት የተቀናጀ የአላህ በረከትና ርህራሄው ለነቢያችን ለሙሐመድ ለቤተሰቦቻቸውና ለሰሓቦቻቸው ሁሉ ይሁን።

ሙሐመድ ብን ሷሊሕ ብን ዑሠይሚን

## ተውበት (ንስሐ)

**ተውበት**:- በአላህ (ሱወ) ትእዛዝ ላይ ከማመጽ (ከመዕስያ) ለሕግጋቱ ወደ መታዘዝ (ጣዓህ) መመለስ ነው።

**ተውበት**:- ተውበት አላህ (ሱወ) ዘንድ በጣም የተወደደ ነው:-

﴿إن الله يحب التوابين ويحب المتطهرين﴾

«...አላህ (ከኃጢአት) ተመላሾችን ይወዳል! ተጥራሪዎችንም ይወዳል፥..»[2]

**ተውበት**:- በያንዳንዱ አማኝ ላይ ግዴታ (ዋጅብ) ነው:-

﴿يا أيها الذين آمنوا توبوا إلى الله توبة نصوحًا﴾

---

1 አል–ተውባህ (9):113

2 አል–በቀራህ(2):222

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ንጹሕ የኾነችን ጸጸት በመጸጸት ወደ አላህ ተመለሱ!..»[1]

ተውበት:- ከመድህን ማስገኛ ምክንያቶች አንዱ ነው:-

وَتُوبُوٓاْ إِلَى ٱللَّهِ جَمِيعًا أَيُّهَ ٱلْمُؤْمِنُونَ لَعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ ﴿٣١﴾

«..ምእመናኖች ሆይ! ትድኑ ዘንድ ሁላችሁም ወደ አላህ (በመመለስ) ተጸጸቱ።»[2]

መድህን (ፈላሕ) ማግኘት ማለት ያንድ ሰው የፈለገውን ማግኘት ከሚፈራው ነገር መዳን ነው።

ፍጹምና እውነተኛ የሆነ ተውበት:- የፈለጋቸውን ያህል ቢከብዱና ያሻቸውን ያህል ቢበዙ እንኳ አላህ (ሱወ) ፍጹምና እውነተኛ በሆነ ተውበት ኃጢአቶችን ሁሉ ይቅር ብሎ ምሕረት ያደርጋል:-

﴿قل يا عبادي الذين أسرفوا على أنفسهم لا تقنطوا من رحمة الله إن الله يغفر الذنوب جميعًا إنه هو الغفـور الرحيم﴾.

«በላቸው እናንተ በነፍሶቻችሁ ላይ ድንበር ያለፋችሁ ባሮቼ ሆይ! ከአላህ እዝነት ተስፋ አትቁረጡ፤ አላህ ኃጢአቶችን በመላ ይምራልና፤ እነሆ እርሱ መሓሪው አዛኙ ነውና።»[3]

ኃጢኡ ወንድሜ! ከጌታህ እዝነት ተስፋ አትቁረጥ፣ የተውበት በር ጸሐይ በመጥለቂያዋ በኩል ተመልሳ እስከምትወጣበት ጊዜ ድረስ ክፍት ነውና።

¤ ነቢዩ (ሰዐወ) እንዲህ ብለዋል:-

قال النبي ﷺ : «إن الله يبسط يده بالليل ليتوب مسيء النهـار ويبسط يده بالنهـار ليتوب مسيء الليل حتى تطلع الشمس من مغربها» رواه مسلم.

---

1 አል–ተሕሪም (66):8

2 አል–ኑር (24):31

3 አል–ኑር (24):31

«ቀን ጥፋት የሰራ ሰው ተጸጽቶ ይመለስ ዘንድ አላህ እጁን ሌሊት ይዘረጋል፣ ሌሊት ጥፋት የሰራ ሰው ተጸጽቶ ይመለስ ዘንድም እጁን ቀን ይዘረጋል፤ (ይህም) ጸሐይ ከመጥለቂያዋ በኩል ተመልሳ እስከወጣችበት ጊዜ ድረስ ነው።»[1]

በፈጸሙት ብዙና ከባድ ኃጢአቶች ተጸጽተው ወደርሱ የተመለሱ የስንትና ስንቱን ጸጸት አላህ ተቀብሏል።

- አላህ (ሱወ) እንዲህ ብሏል:-

قال الله تعالى: ﴿والذين لا يدعون مع الله إلهًا آخر ولا يقتلون النفس التي حرم الله إلا بالحق ولا يزنون ومن يفعل ذلك يلقى أثامًا يضاعف له العذاب يوم القيامة ويخلد فيه مهانًا إلا من تاب وآمن وعمل عملاً صالحاً فأولئك يبدل الله سيئاتهم حسنات وكان الله غفوراً رحيمًا﴾.

«እነዚያም፥ ከአላህ ጋር ሌላን አምላክ የማይገገዙት፤ ያችንም አላህ እርም ያደረጋትን ነፍስ ያለ ሕግ የማይገድሉት፤ የማያመነዝሩትም ናቸው፤ ይህንንም የሚሰራ ሰው ቅጣትን ያገኛል። በትንሣኤ ቀን ቅጣቱ ለርሱ ይደረባል፤ በርሱም ውስጥ የተዋረደ ኾኖ ይኖራል። ተጸጽቶ የተመለሰና ያመነ፥ መልካምንም ሥራ የሠራ ሰው ብቻ ሲቀር፤ እነዚያም አላህ መጥፎ ሥራዎቻቸውን በመልካም ሥራዎች ይለውጣል፤ አላህም እጅግ መሓሪ አዛኝ ነው።»[2]

ፍጹምና እውነተኛ የሆነ ጸጸት (ተውበት አን–ነሱሕ) አምስት መሥፈርቶችን ያሟላ ነው:-

አንደኛ– ለአላህ (ሱወ) ፍጹም መሆን ሲሆን ይህም ተጸጽቶ የሚመለሰውና ተውበት የሚያደርገው ለአላህ (ሱወ) ብሎ ምንዳውን ለማግኘትና ከቅጣቱ ለመዳን በማቀድ መጸጸት ማለት ነው።

---

1 ሙስሊም የዘገቡት

2 አል–ፉርቃን (25): 68–70

ሁለተኛ– በሠራው ጥፋትና በፈጸመው ኃጢአት በመጸጸት ባልሰራሁት ብሎ ባለፈው ድርጊቱ ማዘን።

ሦስተኛ– ከኃጢአቱ ወዲያውኑ መወገድና ከነጭራሹ እርግፍ አድርጐ መተው። የተፈጸመው ጥፋት ከአላህ (ሱወ) መብት ጋር የተያያዘ፣ የተከለከለና ሐራም የሆ ነገር ሠርቶ ከሆነ ወዲያውኑ ማቆም፣ ማድረግ የነበረበት ነገር ትቶ ከሆነም ወዲያውኑ ወደ ሥራው መሰማራት ነው። ጥፋቱ ከፍጡራን መብት ጋር የተያያዘ ከሆነም ራሱን ወዲያውኑ ከዚያ ነገር ነጻ ማድረግ ነው። ይህም ወይም የሚመለስ ነገር ከሆነ ለባለመብቱ በመመለስ ወይም ጥፋት የተሰራበትን ሰው ፍጹማዊ ይቅርታና ልባዊ ምሕረት በመጠየቅ ይሆናል።

አራተኛ– ወደፊት ወደኋላ ኃጢአት ጭራሽ ላለመመለስ ቁርጠኛና ጽኑ አቋም መውሰድ።

አምስተኛ– ተውበቱ ዐይ በዕድሜው ፍጻሜ መድረስ ምክንያት ወይ ደግሞ ጸሐይ በስተምዕራብ በኩል ተመልሳ በመውጣቷ የተወቡት መቀበያ ጊዜው ያላለፈ መሆን። አላህ (ሱወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿وليست التوبة للذين يعملون السيئات حتى
إذا حضر أحدهم الموت قال إني تبت الآن﴾

«ጸጸትንም መቀበል ለነዚያ ኃጢአቶችን ለሚሠሩ፥ አንዳቸውንም ሞት በመጣበት ጊዜ እኔ አሁን ተጸጸትኩ ለሚልና...አይደለችም።..»[1]

¤ ነቢዩም (ሰዐወ) እንዲህ ብለዋል:-

«من باب قبـــل ان تطلع الشمس من مغربها تاب الله عليه»
رواه مسلم.

«ጸሐይ ከመጥለቂያዋ በኩል ተመልሳ ከመውጣቷ በፊት ከሠራው ኃጢአት ተጸጽቶ የተመለሰ ሰው አላህ ጸጸቱን ይቀበላል።»[2]

አላህ ሆይ! እውነተኛ የሆነ ልባዊ ተውበት አሳካልንና ከኛም ተቀበለን፤ አንተ ሰሚውና በጣም ዐዋቂው ነህና።

---

1 አል–ኒሳእ (4):18

2 ሙስሊም የዘገቡት ሐዲሥ

# ምዕራፍ 3

# የቀብር ሥነ–ሥርዓት

* የሞተ ሰው አስተጣጠብ ሕጐች
* የአስተጣጠቡ ሁኔታ
* .የአገናነዙ ሁኔታ
* እንዴት እንደሚሰገድበት
* የአቀባበሩ ሁኔታ

# የሬሳ አስተጣጠብን የሚገዙ ሕጎች

ምሥጋና የዓለማት ጌታ ለሆነው አላህ ይድረስ። ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ አለመኖሩንና እርሱ አንድና ሸሪክ የሌለው፣ የቀደምቶችና የመጪዎች ሁሉ አምላክ መሆኑን እመሰክራለሁ። የነቢዩች መደምደሚያና የፈራሂያን መሪ የሆኑት ሙሐመድ የርሱ አገልጋይና መልዕክተኛው መሆናቸውን እመሰክ ራለሁ። የአላህ ከአክብሮት የተቀናጀ እዝነትና ሠላሙ ለርሳቸው፣ ለቤተሰ ባቸው ለባልደረቦቻቸውና እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ በቅንነት ፈለጋቸውን ለተከተሉ ሁሉ ይሁን።

ከዚህ ቀጥዬ የማቀርባት:- ይህች የሬሳ አስተጣጠብን፣ አገናነዙንና አቀባበሩን የምትመለከት አጭር ጽሑፍ ነች። ወደ ርዕሱ ከመግባታችን በፊት ቀጥሎ ያሉትን ነጥቦች እናስቀድማለን:-

1. የሙስሊሙን ሬሳ ማጠብ፣ መገነዝና መቅበሩ ፈርድ አል–ከፋያ (የወል ግዴታ) ነው። ስለዚህም ግዴታውን የሚፈጽም ሰው ከአላህ (ሱወ) ምንዳና ሽልማቱን ለማግኘት ይህን ግዴታ ለመተግባር ቁርጥ ውሳኔ (ኒያ) በማድረግ መጀመር ይገባዋል። ሙስሊም ያልሆነ ከሐዲ (ካፊር) ሬሳ ግን ማጠቡም ሆነ መገነዙ፣ በሙስሊሞች መካነ መቃብር መቅበሩም አይፈቀድም።
2. አጣቢው ለሟቹ ታማኝና ኃላፊነት የተጣለበት በመሆኑ በማጠቡም ሆነ በሌላው ማድረግ ያለበትን ማድረግ ግዴታ (ዋጅብ) ይሆንበታል።
3. አጣቢው ለሟቹ ታማኝና ኃላፊነት የተጣለበት በመሆኑ በሬሳው ላይ ያየውን ጥሩ ያልሆነ ነገር የመሸሸግ ግዴታ አለበት።
4. አጣቢው ሰው ለሟቹ ታማኝና አመኔታ የተጣለበት በመሆኑ በሚያጥብበት ጊዜ አስከሬኑን ለማገላበጥ፣ ውሃ ለመጨመርና ለመሳሰሉት ነገሮች ለማገዝ አስፈላጊ ከሆነ ሰው በስተቀር ማንም ሰው አጠገቡ እንዲገኝ ማድረግ አይገባውም።
5. አጣቢው ሰው ለሟች ታማኝና አመኔታ የተጣለበት በመሆኑ አስከሬኑን ለማጠብ ልብሱን ሲያወልቅለት፣ ሲያጥበውና በሁሉም ሁኔታ በጥንቃቄ፣ በርህራሄ፣ በቀስታና በከበሬታ መስራት እንጂ ማንገላታትና ሀይልን የሚጠቀም መሆን የለበትም።

6. ሟች ሚስቱ ካልሆነች በስተቀር ወንድ የሴት ሬሳ አያጥብም። ሴትም እንደዚሁ ባልዋና ከሰባት ዓመት ያነሰ ልጅ ካልሆነ በስተቀር የወንድ አስ ከሬን አታጥብም። ሟቹ ከሰባት ዓመት በታች የሆነ ወንድ ከሆነ ሴትም ሆነ ወንድ ሬሳውን ማጠብ ይችላል።

7. አጣቢው አጥቦ ካበቃ በኋላ ለጀናባ በሚታጠበው ዓይነት ገላውን መታጠብ የተወደደ (ሙስተሐብ) ሲሆን ባይታጠብም ችግር የለውም።

## ሬሳ እንዴት እንደሚታጠብ

ሬሳ ሲያጥቡ ዋጅቡ ሙሉ አካሉን እስኪጸዳ ድረስ በውሃ ማጠብ ነው። በላጩ ግን ቀጥሎ የተመለከተውን ማድረግ ነው:-

1. ሬሳውን በሚያጥቡበት ሥፍራ ላይ ወደ እግሮቹ በኩል ትንሽ ያዘቀዘቀ አድርጐ ማኖር።
2. ልብሱን ከማውለቅ በፊት ሀፍረተ ገላው (ዐውረቱ) እንዳይታይ ከእምብርቱ እስከ ጉልበቱ መካከል ያለውን በሚሸፍን ጨርቅ መጠቅለል።
3. የሟቹን ልብስ በጥንቃቄ ማውለቅ።
4. አጣቢው በእጁ ላይ ጨርቅ በመጠቅለል የሟቹን ሀፍረተ ገላ ሳይገልጥ ባለበት እጁን አስገብቶ አጽድቶ ያጥብና በእጁ ላይ የጠቀለለውን ጨርቅ አውቆ መጣል።
5. ቁራጭ ጨርቅ በውሃ በማርጠብ የሟቹን ጥርሶችና የአፍንጫውን ቀዳዳዎች ማጽዳት።
6. የሟቹን ፊት፣ ሁለት እጆቹን እስከ ክርን ድረስ፣ ራሱን፣ ሁለት እግሮቹን እስከ ቁርጭምጭሚቶች ድረስ በቀኝ ጀምሮ ቀኙን ከግራው በማስቀደም ማጠብ።
7. ወደ ሟቹ አፍም ሆነ ወደ አፍንጫው ውኃ አያስገባም። በጨርቁ በማጽዳት ብቻ መወሰን።
8. ሙሉ ገላውን ሦስት ጊዜ ወይም አምስት ጊዜ ወይም ሰባት ጊዜ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ከዚህም በላይ በመጨመር ገላው እስኪጸዳና እስኪጠራ ድረስ ከግራ አካሉ በፊት በቀኝ በኩል በመጀመር ማጠብ።
9. የሚያጥብበትን ውሃ በቁርቁራ (ሲድር) መቀላቀሉ የበለጠ የሚያጠራ በመሆኑ ይመረጣል። ይህን ሲያደርግም ከቁርቁራ ጋር የተበረዘውን ውሃ

አረፋ እስኪወጣው ድረስ በእጅ ይመታና በአረፋው የሬሳውን ራስና ጺሙን በተቀረውም ሌላውን አካሉን ያጥብበታል።

10. በመጨረሻው ዙር እጥበት (ካፉር) (ጥሩ መዓዛ ያለው የታወቀ ተክል) መቀላቀሉ በላጭ ነው።

11. ሟቹ ጸጉር ካለው አጣቢው ያበጥረዋል፤ አይደመድመውም፤ ምንም አይቆርጥበትም።

12. ሟች ሴት ከሆነች የተጉነጐነ ጸጉሯ ይፈታል። ከታጠበ በኋላ ሦስት ቦታ ተጉንጉኖ ወደ ጀርባዋ ይለቀቃል።

13. ከሟቹ የአካል ክፍሎች የተለያዩ ካሉ ይታጠቡና ወደ አካሉ ይመለሳሉ።

14. የሟች አካል በእሳት ቃጠሎና በመሳሰሉት ነገሮች ሳቢያ የተበታተነ ሆኖ ለማጠብ የማይመች ከሆነ በብዙዎች ሊቃውንት አቋም መሠረት ተየሙም ይደረግለታል። ተየሙም የሚያደርግለት ሰው እጆቹን መሬት ላይ በማሳረፍ በሁለት መዳፎቹ የሟቹን ፊትና እጆች ያብሳል።

## ሬሳ እንዴት እንደሚገነዝ

የመገነዝ ግዴታ (ዋጅቡ) የሬሳውን ገላ ሙሉ በሙሉ በሚሸፍን ጨርቅ መጠቅለል ነው። ይበልጥ የሚመረጠው ግን የሚከተለው ነው:-

1. በሦስት ነጫጭ ጨርቆች አንዱን ከሌላው ላይ አድርጎ አስከሬኑን በላዩ—ላይ በማድረግ ከሟቹ የቀኝ ጐን በኩል ያለውን የጨርቁን ጫፍ ወደ ደረቱ ማጠፍና ከዚያም በግራ ጐኑ በኩል ያለውንም ወደ ደረቱ መጠቅለል ነው። ከዚያም ሁለተኛውን ጨርቅና ሦስተኛውንም ጨርቅ በዚህ ሁኔታ ተራ በተራ ወደ ደረቱ መጠቅለል ነው። ከዚያም የጨርቆቹን ጫፎች ከላይ በአናቱ ላይ ከታችም ከእግሮቹ ላይ ማሰር ነው።

2. የመገነዣ ጨርቆች በእጣን ይታጠኑና በተለይ ለዚህ የተዘጋጀ ሽቶ (ሐኑጥ) በየጨርቁ መካከል ይነሰነሳል።

3. ከሽቶው በአስከሬኑ ፊት በብብቶቹና በሱጁድ መውረጃ አካሎቹ ላይ ይነሰነሳል።

4. ከሽቶው በጥጥ ተደርጎ በዐይኖቹ ላይ በአፍንጫው ቀዳዳዎችና በከንፈሮቹ ላይ ይደረጋል።

5. ከሽቶው ጥቂት በጥጥ ተደርጎ በሁለት ጭኖቹ መካከል ይደረግና በጨርቅ ይታሰራል።

6. ሴት በአምስት ጨርቆች:- ከወገብ በታች የሚለበስ ግልድም (እዛር)፣ ቀሚስና ሁለት ብትን የመጠቅለያ ጨርቆች ትከፈናለች። ወንድ በሚገነዘበት ዓይነት ብትገነዘም ችግር የለውም።

7. የመገነዣው ቋጠሮዎች ሬሳው መቃብር ውስጥ ሲደረግ ይፈታሉ።

## በሬሳ ላይ እንዴት እንደሚሰገድ

1. በሙስሊም አስከሬን ላይ ትንሽም ይሁን ትልቅ፣ ወንድም ይሁን ሴት በሁሉም ላይ ይሰገዳል።

2. አራት ወር የሞላው ጽንስ ሞቶ ከወጣ ለትልቅ ሰው የሚደረገው ሥነ ሥርዓት ሁሉ ይደረግለታል። ይታጠባል፤ ይገነዛል፤ ይሰገድበታል።

3. አራት ወር ከመሙላቱ በፊት ከሆነ ግን ነፍስ (ሩሕ) ስለማይነፋበት አይታጠብም፣ አይገነዝም። መደረግ ያለበት በሆነ ቦታ መቅበር ብቻ ነው።

4. ሶላቱ በሚሰገድበት ጊዜ ኢማሙ በወንዱ አስከሬን በራሱ አቅጣጫ በኩል ሴት ከሆነች ደግሞ በወገቧ አቅጣጫ በኩል ይቆምና ሰዎች ከኢማሙ ጀርባ ሆነው ይሰግዳሉ።

5. በሬሳ ላይ ሲሰገድ አራት ተክቢራ (አሏሁ አክበር) ይደረጋል። ከመጀመሪያው ተክቢራ በኋላ ከ ‹ተዐውዝ› (አዑዙ ብልላሀ...) እና ከ ‹በስመላ› (ብስምልላሀ..) በኋላ ፋቲሐ ይነበባል። ከዚያም ሁለተኛ ተክቢራ ተደርጐ ‹አልሏሁምመ ሶልሊ...› የሚለው የአትተሕይያቱ (ተሸሀሁድ) ክፍል ‹..ወዐላ አል ኢብራሂመ እንነከ ሐሚዱን መጂድ› እስከሚለው ድረስ ያለው ይነበባል። ከዚያም ሰጋጁ ሦስተኛውን ተክቢራ ያደርግና ለሟቹ ዱዓእ (ጸሎት) ይደረግለታል። ይበልጥ የሚመረጠው ከነቢዩ (ሰዐወ) ከተላለፉት ጸሎቶች በአንደኛው ቢደረግ ነው። ያን ካላወቀ ግን በሚያውቀው ዓይነት ዱዓእ ያደርግለታል። ከአራተኛው ተክቢራ በኋላ ትንሽ ቆም ይልና በሠላምታ ሶላቱን ያበቃል። ከሰላምታ በፊት:-

ربنا آتنا في الدنيا حسنة وفي الآخرة حسنة وقنا عذاب النار فلا بأس بذلك

«ረብበና አትና ፊድዱንያ ሐሰነተን፣ ወፊል–አኺረቲ ሐሰነተን ወቅና ዐዛበን–ናር።» ካለም ምንም የለበትም።

# አስከሬን እንዴት እንደሚቀበር

1. ዋጅቡ (ግዴታው) የአስከሬኑ ፊቱ ወደ ቅብላ ተደርጎ ከአውሬ በሚጠብቀው ጉድጓድ ውስጥ መቅበር ሲሆን መቃብሩ ይበልጥ ጥልቅ በሆነ ቁጥር ይበልጥ የተሻለ ይሆናል።
2. በላጩ መቃብሩ (ለሕድ) መሆኑ ነው። ይህም ጉድጓዱ ወደ ታች ከተቆፈረ በኋላ በቅብላ አቅጣጫ ወደ ውስጥ ተፈልፍሎ የሚዘጋጀው መቃብር ነው።
3. መቃብሩ (ሸቅ) መሆንም ይችላል። ይህ ደግሞ የመሬቱ አፈር ረግረግ ያለና ያልጠበቀ ሆኖ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መቃብሩን ወደታች ከቆፈሩ በኋላ በመሐሉ የሬሳው መቅበሪያ ሌላ ጉድጓድ በመቆፈር የሚዘጋጀው መቃብር ነው።
4. አስከሬኑ መቃብሩ ውስጥ ፊቱን ወደ ቅብላ በማዞር በቀኝ ጐኑ ይደረጋል።
5. ወተት ይፈስበትና አስከሬኑ ላይ አፈር እንዳይደረመስ መካከሉ በጭቃ ተመርጎ ይዘጋል።
6. ከዚያ በኋላ ጉድጓዱ ይደፈንና ከመሬት ወለል በላይ ከፍ እንዲል አይደረግም፤ በስሚንቶም ሆነ በኖራ ወይም በሌላ አይገነባም።
7. በሦስት ወቅቶች አስከሬን መቅበር አይፈቀድም። ጧት ጸሐይ ስትወጣ በዓይን እይታ የጦር ዘንግ ያህል ከፍ እስከትል ድረስ፣ ቀን በቀትር ከአናት ላይ ስትሆንም ወደ ምዕራብ አለፍ እስክትል ድረስና ስትጠልቅም በዓይን ግምት የጦር ዘንግ ርቀት ያህል ሲቀራት እስከትጠልቅ ድረስ። የመጀመሪያውና የመጨረሻው የጊዜ መጠን ሩብ ሰዓት ያህል ሲሆን የሁለተኛው ጊዜ ደግሞ ሰባት ደቂቃዎች ያህል ነው።
8. ካፊር በሙስሊሞች መካነ መቃብር አይቀበርም። አይታጠብም፣ አይገነዝም፤ አይሰግድበትምም። የሚቀበረው አስከሬኑ ወደ አገሩ እስኪዛወር ድረስ የማንም ንብረት ባልሆነ ሥፍራ ነው።

ምሥጋና የዓለማት ጌታ ለሆነው አላህ ይድረስ። በአክብሮት የታጀበ የአላህ እዝነት፣ በረከቱና ሠላሙ ለነቢያችን ለሙሐመድ፣ ለቤተሰባቸውና ሰሓቦቻቸው ሁሉ ይሁን።

የአላህ ከጃይ ደሃው
ሙሐመድ አስሷሊሕ አል–ዑሠይሚን
ጻፈው

# الطهارة والصلاة والجنائز

اللغة الأمهرية (أثيوبيا)

لفضيلة الشيخ

**محمد بن صالح العثيمين**

إصدار

المكتب التعاوني للدعوة والإرشاد وتوعية الجاليات بالمعذر وأم الحمام

تحت إشراف وزارة الشؤون الإسلامية والأوقاف والدعوة والإرشاد

ت: ٤٨٢٦٤٦٦ فاكس: ٤٨٢٧٤٨٩ ص.ب: ٣١٠٢١ الرياض: ١١٤٩٧

٢٠